በበኒሻነጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት የክልል ምክር ቤት

ልሳነ ሕግ ጋዜጣ

LISSANE HIG GAZETA

Of the Council of the Benishangul Gumuz Regional State

14ኛ ዓመት ቁጥር 85
አሶሳ መስከረም 2002

በቤኒሻነጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግግስት
በክልል ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

Issued Under the Auspice of the Council of
Benishangul Gumuz Regional State

14Th Year No.85
Assosa.......September, 2010

## አዋጅ ቁጥር 85 /2002

## የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ

የገጠር መሬትን በአግባቡና በእንክብካቤ በመጠቀም ለምነቱን ጠብቆ ለመጭው ትውልድ ማስተላለፍ እንዲቻል አስተዳደሩንና አጠቃቀሙን ወስኖ በሕግ መደንገግ አስፈላጊ መሆኑን በመገንዘብ፤

ለገጠር መሬት ተጠቃሚዎች የመሬት ይዞታ ዋስትና በመስጠት መብትና ግዴታቸውን አውቀው ለያዙት መሬት ተገቢውን እንክብካቤ በማድረግ መጠቀም እንዲችሉ ምቹ ሁኔታ መፍጠሩ አስፈላጊ በመሆኑ፤

መሬትና የመሬት ሃብትን በጥናት ላይ ተመስርቶ በሚወጣ ዕቅድ ለመጠቀም፣ መሬትን አስመልክቶ ለሚነሱ ግጭቶች፣ አለመግባባቶች እና የአጠቃቀም ችግሮች ሕግን መሠረት ያደረገ የመፍትሄ እርምጃ መውሰድና የቁጥጥርና የአስተዳደር ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤

## Proclamation No. 85 /2010

## Benishangul Gumz Regional State Rural Land Administration and Use Proclamation

WHEREAS, it is found necessary to determine and provide the rural land administration and use to maintain its fertility and to be able to transfer to the next generation by using it properly and carefully;

WHEREAS, by giving security of land possession for rural land users, and it is necessary to create conducive environment so as to enable them to make the proper care for the land they possess by knowing their rights and duties;

WHEREAS, using land and its resource according to plan, establishing legal system for administering, and controlling measures to be taken for solving disputes, controversy and problems to utilization arises on using the land and the resource of the land is required.

የሴቶችን የመሬት ይዞታ ባለቤትነትና የመጠቀም መብት ያለምንም ተጽዕኖ ማረጋገጥ በማስፈለጉ፤

መሬትና የተፈጥሮ ሀብትን ለማስተዳደር በፌዴራሉ ሕገ መንግሥት ለክልሎች በተሰጠው ሥልጣን መሠረት አርሶ አደሩ፣ ባለሀብቱና አግባብ ያላቸው ድርጅቶች መሬትን በአግባቡ በማልማት በመጠቀምና በመጠበቅ የሚኖራቸውን ተሳትፎ ለማጠናከርና ከመንግሥት የልማት ዓላማዎች ጋር እንዲቀናጅ ለማድረግ የሚያስችልና በክልሉ ተጨባጭ ሁኔታዎች ላይ የተመሠረተ ሥርዓት ቀርጾ በሥራ ላይ ማዋል እንደሚያስፈልግ በማመን፤

የክልሉ ህገ መንግስት ለህዝብና ለመንግስት የሰጠውን የመሬት ባለቤትነት መብት በተግባር በመተርጎም እያንዳንዱ መሬት ተጠቃሚ በተለይም የአርሶ አደሩን የመሬት ባለይዞታነት፣ የመጠቀም መብትና ግደታውን በመወሰን ለመሬቱ አስፈላጊውን እንክብካቤ በማድረግ እንዲጠቀም ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በክልሉ ህግ-መንግሰት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3(1) መሠረት የሚከተለው ታውጃዋል።

WHEREAS, it is needed to insure women’s land possession and use right with out any undue influence;

WHEREAS, it is believed that to design and implement a system based on objective realities of the region pursuant to the power vested to the regions by the federal constitution administer the land and the natural resources and strengthen the farmer, the investor and appropriate organizations in their participation to use land maintaining it properly, use and keep, and to coordinate it with the development objectives of the government.

WHEREAS, to translate the power vested to the people as to the owner ship of the land and for land users in conserving and take care of the land by knowing their rights and duties;

NOW, THEREFORE, in accordance with sub-article 3(1) of Article 49 of the regional constitution, its where by here proclaimed as follows.

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1 **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል የገጠር መሬት አሰተዳደርና አጠቃቀ መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 85../2002 ዓ/ም» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1. የገጠር መሬት» ማለት ከማዘጋጃ ቤት ክልል ውጪ ወይም አግባብ ባለው ህግ "ከተማ" ተብሎ ከሚሰየመው ውጪ ያለ ማንኛውም መሬት ነው፡፡
2. የገጠር መሬት አስተዳደር» ማለት በገጠር መሬት ይዞታ ላይ ዋስትና የሚሰጥበት፣ የገጠር መሬት አጠቃቀም ዕቅድ የሚተገበርበት፣ በገጠር መሬት ተጠቃሚዎች መካከል የሚነሱ አለመግባባቶች የሚፈቱበትና የማንኛውም የገጠር መሬት ተጠቃሚ መብቶችና ግዴታዎች የሚተገበሩበት፣ እንዲሁም የባለይዞታዎች ማሣዎችን፣ የግጦሽ መሬትን መረጃ በመሰብሰብና በመተንተን ለተጠቃሚዎች እንዲደርሱ የሚደረግበት ሂደት ነዉ።
3. የገጠር መሬት አጠቃቀም» ማለት የገጠር መሬትን በእንክብካቤ ይዞ ዘላቂነት ባለው መንገድ ለተሻለ ጠቀሜታ እንዲውል የሚደረግበት ሂደት ነው፡፡

## PART ONE

## GENERAL

**1 SHORT TITLE**

This proclamation may be cited as the Benishangul Gumuz Regional state Land Administration and use proclamation number … /2010

**2. Definition**

Unless the context otherwise requires, in this proclamation

1. ”Rural land” means land outside the boundaries of a municipality or outside an area which is designated as a town by the pertinent law.
2. ”Rural land administration” means rules and procedures on rural land and this proclamation by which agreements between land users and any rights and duties of them, system of land distribution by the proper procedure, protection of land, giving guarantee on possession of land, land use plan implementation and conflict resolution among users is executed.
3. ”Rural land use” the rural land held appropriately and use for better services on a sustainable basis.

4. የይዞታ መብት» ማለት ማንኛውም አርሶ አደር ወይም በአዋጁ መብት የተሰጠው ሌላ ማናቸውም አካል በዚህ አዋጅ መሠረት የተረጋገጡለትን የመሬት ባለይዞታ የመሆን፣ በመሬቱ ላይ ንብረት የማፍራት፣ ያፈራውን ንብረት የማስተላለፍ፣ ከይዞታ መሬቱ ያለመነቀል፣ መሬቱን ለግብርናና ለተፈጥሮ ሃብት ልማትም ሆነ ለሌሎች ተግባራት የማዋል፣ የመጠቀም፣ መሬቱን የማከራየት፣ የማውረስ፣ በስጦታ የማስተላለፍና የመሣሰሉትን መብቶች የሚያጠቃልል ነው፡፡

5. የቤተሰብ አባል» ማለት ከመሬት ባለይዞታው ጋር በቋሚነት አብሮ የሚኖርና የራሱ የሆነ ቋሚ መተዳደሪያ የሌለው የይዞታ ባለመብቱን ገቢ በመጋራት የሚተዳደር ማንኛውም ሰው ነው፡፡

6. የገጠር መሬት አጠቃቀም ዕቅድ» ማለት አካላዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ መረጃዎችን መሠረት በማድረግ የገጠር መሬት መጐሣቆልና የአካባቢ ብክለት ሣይደርስበት መሬት ሊሰጥ ከሚችላቸው አማራጭ ጥቅሞች የተሻለው ተመርጦ ተግባራዊ የሚደረግበት ሥርዓት ሲሆን ስልታዊና የአካባቢ ልማት ዕቅዶችን ያጠቃልላል፡፡

7. «አርሶ አደር» ማለት መደበኛ ወይም ቋሚ መተዳደሪያው የግብርና ሥራ የሆነ ማናቸውም ሰው ነው፡፡

8. የግብርና ሥራ ማለት፤ የሰብል ልማት፤ የእንስሳት ልማት የደን ልማትና የመሳሰሉትን ያጠቃልላል፡፡

4. "Possession right" any peasant or anybody who has right on proclamation, by this proclamation it is ascertained to be land holder, to produce properly on the land, transferring the property, not to be deprived from the land, to use the land for agricultural and natural resource development and the likes.

5."Family member" anyone who lives permanently with a person having a holding right by sharing the means of the livelihood of the holder.

6."Rural land use plan" a plan which is based on physical, economic and social data with out causing land degradation and environmental pollution and the best use of the land among the alternative use thereof: are made applied based on thse and shall include the activities, using right, land rent, transferring by bequesing and donation are included.methodological and environmental plan.

7."Peasant or Farmer" anyone who permanentely earns the livelihood by agricultural means.

8. Agricultural activities includes crop production, animal husbandary, forestry and the likes.

9. የመሬት ተጠቃሚ ማለት የገጠር መሬትን የመገልገልና በምርቱ የመጠቀም መብት የተሰጠው ማንኛውም ሰው ነው::

10. አነስተኛ የይዞታ መጠን" ማለት ምርታማነቱ የአንድን አርሶ አደር የምግብ ዋስትና ሊያረጋግጥ የሚችል የገጠር መሬት ይዞታ ወይንም ለሰብል እርሻ፣ ለቋሚ ሰብል፣ ለግጦሽ፣ ለመኖሪያ ቤትና ለጓሮ አትክልት ልማት በቂ ነው ተብሎ በይዞታነት የሚሰጥ ዝቅተኛ የመሬት መጠን ነው::

11. አነስተኛ የማሣ መጠን" ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ ደንብ የሚወሰንና ለአንድ ሰው በይዞታነት የሚሰጥ ዝቅተኛ የአንድ ማሣ ስፋት ነዉ፤፤

12. "የግል ይዞታ" ማለት በማንኛውም አርሶ አደር ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት የመጠቀም መብት በተሰጠው ሌላ አካል እጅ ሆኖና የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ወጥቶለት በግል ይዞታ ሥር የሚገኝ የገጠር መሬት ነው::

13. "የጋራ ይዞታ" ማለት ቁጥራቸው ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች በአንድ መሬት ላይ ያልተከፋፈለ የይዞታ ባለመብቶች ሆነው መሬቱን ሳይከፋፈሉ ከዚሁ ከመሬቱ የሚገኘውን ጥቅም እየተጋሩ የሚጠቀሙበት የገጠር መሬት ነው::

14. "የወል ይዞታ" ማለት ከመንግሥት ወይም ከግል ይዞታነት ውጭ የሚገኝና የአካባቢው ነዋሪዎች በህብረት የሚጠቀሙበት መሬት ሲሆን ለግጦሽ፣ ለደንና ለሌሎች ማህበራዊ አገልግሎቶች የዋለ የገጠር መሬት ነው::

9. "Land user" anyone who utilizes the land have the right to benefit from the production.

10. . "Minimum holding Size" holding of land size sufficient enough including crop cultivation, perennial crops, grazing, residential and backyards to sustain the life of one peasant.

11. "Small plot size" means the minimum plot of land to be given to a person in holding and shall be determined by regulation to be issued pursuant to this proclamation

12. "Private holding "a land possessed by any farmer or other body vested with right to use and existing under private holding having a certificate.

13. "Common Holding" holding of land by two or more persons in common having the holding right, and use without division, by sharing the output from the land.

14. "communal holding" a land out of government or individual possession and is being under the common holding for grazing, forest and other social services.

15. የመንግሥት ይዞታ» ማለት ለአገርና ለአካባቢ ልማትና እድገት ተብሎ በመንግሥት ይዞታነት በፌዴራልም ሆነ በክልል ደረጃ የተያዘ መሬት ሲሆን ጥብቅ የደን መሬቶችን፣ የዱር እንስሳት መጠለያዎችን፣ የማዕድን ማውጫ ቦታዎችን ፓርኮችንና በሃይቆችም ሆነ በወንዞች አካባቢ የሚገኙ ሥፍራዎችን ያጠቃልላል፡፡

16. «የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር» ማለት በገጠር መሬት የመጠቀምን መብት ለማረጋገጥ አግባብ ባለው አካል የሚሰጥ ሠነድ ነው፡፡

17. «የመሬት ምዝገባ» ማለት የገጠር መሬትን በተመለከተ የሚገኝበትን ቦታ፣ ስፋቱን፣ አዋሣኞቹን፣ የለምነቱን ደረጃና የባለይዞታውን ማንነት ጨምሮ የተሟላ መረጃ በመዝገብ ላይ የማስፈርና የማጠናከር ሂደት ነው፡፡

18. «የመሬት መረጃ ስርዓት» ማለት የገጠር መሬት ነክ መረጃዎችን ማሰባሰብ፣ በመተንተንና በአግባቡ እንዲያዙ በማድረግ ለተለያዩ ተጠቃሚ ክፍሎች የማሰራጨት ስርዓት ነው፡፡

19. «ባለሥልጣን» ማለት የቤኒሻንጉል-ጉሙዝ ክልል የአካባቢ ጥበቃ፣ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ባለሥልጣን ነው፡፡

20. «ሰው» ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

15. ”Government holding”land demarcated and held and could be held by the government and includes large forest lands, wild animals dwell parks, , mining, lakes and rivers.

16. ”Land holding certificate” document given by the authority to ascertain the right to use on land.

17. ”Land registration” an activity of registering the detail information such as the location, area, fertility grade and the identity of the holder on the book concerning the rural land.

18. a system of land registration in which land related information Shall be kept Appropriately an distributed to different users.

19. ”Authority” the Benishangul Gumuz Region Environment Protection, Land Administration and Use Authority.

20. ”Person” natural or legal person.

21. ልጅ» ማለት በሥጋ የተወለደ ወይም የጉዲፈቻ ልጅ ማለት ነው::

22. «ተጧሪ» ማለት በዕድሜ መግፋት፣ በበሽታ፣ በአካል ጉዳት ወይም በሌሎች ተያያዥነት ባላቸው ምክንያቶች ሳቢያ በራሱ ገቢ ይሚያስገቃ ሥራ መሥራት የተሳነውና ለመተዳደሪያው የሌሎችን ሰዎች ዕርዳታ የሚፈለግ ማንኛውም ሰው ነው::

23. «የቀበሌ ነዋሪ» ማለት መደበኛ መቀመጫውን በአንድ ቀበሌ አድርጎ መሠረታዊ አገልግሎቶቹንና ማህበራዊ ጥቅሞቹን በዚያው ቀበሌ ውስጥ የሚያገቃ ማናቸውም ሰው ነው::

24. «የሕዝብ አገልግሎት» ማለት በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ለሕዝብ አገልግሎት የሚሰጥ እንደ መንግሥት መ/ቤት፣ ትምህርት ቤት፣ የጤና አገልግሎት፣ የገበያ አገልግሎት፣ የመንገድ፣ የሃይማኖት ተቋማት፣ የወታደር ካምኘ የመሳሰሉትና በክልሉ መንግሥት ለሕዝብ እድገት ይጠቀማሉ ተብለው በገጠር መሬት ላይ እንዲፈፀሙ የሚወሰኑ ተግባራትን ያጠቃልላል::

25. «ሌላ ንብረት» ማለት ከመሬት በስተቀር ማናቸውም ሌላ ንብረት ነው::

26. «የመጠቀም መብት» ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት በመሬት የመገልገልና የሚገኘውን ምርት የመጠቀም መብት ነው::

21. "Child" natural or adopted child.

22. "Pensioned" any person who is unable to engage in works that create income by himself and seeks others help for his livelihood due to disease, disability or other related reasons.

23. "Kebele resident" any person who resides in one Kebele and earns the basic services and social benefits in the same.

24. "Public service" a service given to the public directly or indirectly, such as government office, school, health service, market service, road, religious institutions, military camps and the likes, and include activities assumed important to the development of people by the regional government and to be implemented on the rural land.

25. "Another property" any property other than land.

26. "Use right" using the land and its production pursuant to this proclamation.

27. "መሬት ማስለቀቅ" ማለት የገጠርን መሬት ለሕዝብ አገልግሎት ሲባል በመንግሥት አካላት፣ በግል ባለሃብቶች፣ በኀብረት ሥራ ማህበራት ወይም በሌሎች አካላት ልማት እንዲካሄድበት ሥልጣን በተሰጠው የመንግሥት አካል ውሣኔ መሠረት በቅድሚያ ካሣ ክፍሎ እና ለባለይዞታው የማካካሻ ይዞታ በመስጠት ከመሬቱ ባለይዞታ ወይም ተጠቃሚ መውሰድ ማለት ነው::

28. "የመሬት ባለይዞታ" ማለት በአንድ የገጠር መሬት ላይ የይዞታ መብት ያለው ግለሰብ፣ የሰዎች ስብስብ ወይም ሕብረተሰብ፣ የመንግሥት አካል፣ ማህበራዊ ተቋም ወይም ሌላ የሕግ ሰውነት ያለው አካል ነው::

29. "ኪራይ" ማለት አንድ አርሶ አደር በዚህ አዋጅ መሠረት ያገኘውን የመሬት ይዞታ ለሌላ ሰው ለተወሰነ የጊዜ ገደብ በውል ሰጥቶ የአይነት ወይም የገንዘብ ጥቅም እየተቀበለ አገልግሎት ላይ እንዲውል የሚያደርግበት ሥሪት ነው።

30. "ሊዝ" ማለት ማንኛውም ባለሃብት የገጠርን መሬት ለተወሰነ ጊዜና አገልግሎት ከመንግሥት የሚወስድበት አሠራር ሲሆን አግባብ ባለው ሕግ እንደተተረጐመው የመጠቀምና የዕዳ ዋስትና አድርጐ እስከ ማስያዝ የሚደርሱ መብቶች የሚካተቱበት ነው::

27. "exapromatral from the land holding" taking the land from the holder or user for the sake of public interest paying compensation in advance by the government bodies, private investors, cooperative societies or other bodies to undertake development activities by the decision of government bodies vested from power.

28. "Land holding" peasant holding rights on rural land including communal, government organs, social institutions or other legalized bodies.

29. "rent" a system by which a farmer causes the use of his land which he gets it pursuant to this proclamation for the service and another person seeking benefits in kind or cash for a limited period of time in contract.

30. "Lease" a system by which any investor takes a rural land from government for a limited period of time, and as it is interpreted in relevant law, the right to use the land.

31. የመስኖ መሬት" ማለት ባሁኑ ጊዜ በመስኖ እየለማ ያለውና ለወደፊትም በመስኖ ሊለማ የሚችል ውኃ ገብ መሬት ማለት ነው፡፡

32. የመሬት ሽግሽግ ማለት በተለያዩ ምክንያቶች የተነሳ መሬት አልባ ለሆኑ አርሶ አደሮች ወይም የይዞታ መጠን ላነሳቸው አርሶ አደሮች ፍትሃዊነትን ለማረጋገጥ የህብረተሰቡን ጥያቄ መሠረት በማድረግ የሚካሄድ የመሬት ሽንሽና ወይም ድልደላ ሂደት ነው፡፡

33. የእዳ ዋስትና ማለት በሊዝ ሥርዓት የተገኘን የገጠር መሬት የመጠቀም መብት፣ በመሬቱ ላይ የለማውን ሃብት ወይም ሁለቱንም ከሌላ ወገን ጋር በሚደረግ ስምምነት መሠረት መጠቀም መቻል ነው፡፡

3 የጾታ አገላለጽ

በዚህ አዋጅ ውስጥ በወንድ ፆታ የተደነገገው ሁሉ ለሴት ፆታም እኩል ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

4 የአዋጁ ተፈፃሚነት ወሰን

1. ይህ አዋጅ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል በሚገኝ ማንኛውም የገጠር መሬት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

31. "Irrigation land" lands which are irrigated and potentially be irrigated.

32."Land redistribution" redistribution of land to landless or land scarce farmers based on petition of the community.

33. "Mortgage" rural land in lease may secure by mortgage right to use his land or an asset produced on it, or both for the effected period of the lease.

**3. Gender Reference**

The provisions of this proclamation set out in the masculine gender shall also equally apply to femine gender.

**4. Scope of application**

1. This proclamation shall apply to any rural land found in the region.

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ለደን፣ ለዱር እንስሳት ጥበቃ፣ ለብዝሃ ሕይወት ሀብትነት፣ ለተፈጥሮ ሀብትና ለአካባቢ ጥበቃ፣ ለማዕድን ልማትና ለመሳሰሉት የተከለሉ መሬቶችን መንከባከብና ማልማትን በተመለከተ የወጡ ልዩ ልዩ ህጎች እንደየተደነገጉባቸው መስኮች ተፈፃሚነታቸው ይቀጥላል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የገጠር መሬትን በይዞታ የማግኘት፣ የመጠቀም መብት፣ የዋስትና እና በአጠቃቀም ረገድ ስለተጣሉ ገደቦች

### 5. የገጠር መሬት ይዞታ መብት

1. የመሬት ባለቤትነት መብት የመንግሥትና የሕዝብ ነው፡፡ በመሆኑም የመሬት ይዞታን በሽያጭም ሆነ በሌላ ንብረት በመለወጥ ለሌላ ማስተላለፍ አይቻልም፤
2. በክልሉ ውስጥ የሚኖር ማንኛውም አርሶ አደር በፆታም ሆነ በሌላ በማናቸውም ምክንያት ልዩነት ሳይደረግበት መሬት በይዞታ የማግኘት እኩል መብት አለው፤
3. በዚሁ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 የሰፈረው እንደተጠበቀ ሆኖ በክልሉ ውስጥ በህገወጥ መንገድ የገቡትንና የሚገቡትን አርሶአደሮች የመሬት ይዞታ መብት አያስገኝም፡፡
4. በክልሉ ውስጥ የአርሶ አደሮች የገጠር መሬት ይዞታ መብት የጊዜ ገደብ የለውም፤
5. የመሬት አስተዳደር ሥርዓት በሕዝብ ተሳትፎ ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት፤

2. Notwithstanding the provision stated under sub-article1 of this article, special laws shall continue on application, as the fields had been stipulated, concerning the delineated lands for forestry, wild animals, biodiversity resources natural resource and environmental protection, mines development and the likes.

## PART TWO

## RIGHT TO HOLD AND USE RURAL LAND, WARRATY AND RESTRICTIONS IMPOSED REGARDING ITS UTILIZATION

### 5. RIGHT TO HOLD LAND

1. Land is the common property of the state and people and it shall not be subjected to sale or other means of exchange.
2. Any peasant resides in the region shall have the right to hold land irrespective of gender or any other discrimination.
3. Notwithstanding the provision stated under sub-article 2 of this article, any peasant who occupied prior to this proclamation and will occupy land illegally shall have no holding right.
4. There is no time limit for peasant or semi-pastoralist in the region as to their rural land holding right.
5. Land administration shall be implemented through participation of the community.

6. የመሬት አጠቃቀም እቅድ አካባቢን በመንከባከብ ላይ አተኩሮ የሚፈፀም ይሆናል፡፡

7. የመሬት ድልድል በሚካሄድበት ጊዜ ለሴቶች፣ ለወጣቶች፣ ለአቅመ ደካሞችና ለወላጅ አልባ ሕፃናት እንደአስፈላጊነቱ ቅድሚያ እንዲሰጥ የሚያደረግ አሠራር ተፈፃሚ ይሆናል፡፡ ዝርዝር አፈጻጸሙ በደንብ ይወሰናል፡፡

8. ተዳፋትነቱ 45 በመቶና ከዚያ በላይ የሆነ ማናቸውም የገጠር መሬት ለደን፣ ለቋሚ ተክሎች፣ ለእንስሳት መኖ ልማት ወይም ለመሣሰሉት ተግባራት ካልሆነ በስተቀር ለእርሻም ሆነ ለልቅ ግጦሽ እንዲውል አይደረግም፡፡ ሆኖም ይህ ድንጋጌ በእንዲህ ያለው የገጠር መሬት ላይ አስቀድመው የሚገኙ ባለይዞታዎች የአካባቢ ጥበቃንና ዘላቂ የተፈጥሮ ሃብት እንክብካቤን በማይጐዳ አኳኋን መሬቱን ለተጠቀሰው አገልግሎት በባለሙያ ምክር ብቻ እየተረዱና እየታገዙ እንዲጠቀሙበት ይደረጋል፡፡

9. በአንቀጽ9 ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ለሕዝብ አገልግሎትና ለተሻለ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ አገልግሎት ለማዋል ካልሆነ በስተቀር የገጠር መሬት የይዞታ መብት እንዲለቀቅ አይደረግም፤

10. በንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 8 የሰፈረዉ እንደተጠበቀ ሆኖ በድንበር አከላለል፣ በሽግሽግ ወይም በመሳሰሉት ምክኒያቶች ይዞታቸዉ በሌላ ቀበሌ የወደቀባቸዉ አርሶ አደሮች በሁለቱ ቀበሌዎች ስምምነት መሰረት ይዞታ እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፡፡

6. Land use may be applicable based on plan and consideration of environmental protection.

7. The working system that gives priority to women, disables, orphan children, youth shall be executed and shall be determined by the regulation.

8. During land distribution. The detail any rural land, above slope 45% shall not be used for farming and free grazing other than forestry, perennial plants, development of forage for animals and other similar activities. However, this provision shall not be effect on the same rural land priorly seized by the land holders who use it that it doesn't damage the environmental protection and sustainable natural resource care being supported by the expertise advice.

9. Pursuant to sub Art 2 of article 9 of this proclamation, the rural land shall not be expropriated unless to use for public services.

10. According to the provisions stated under sub-article 8 of article 6, any one whose holding falls in other kebele due to delineation, re-distribution and the likes, shall obtain holding right by the conscent of the two kebeles. The detail shall determine by the regulation.

## 6. የገጠር መሬት የማግኘትና የመጠቀም መብት

1. በመሬት አስተዳደር ህግ መሠረት፡-

ሀ. በግብርና ስራ የሚተዳደሩ አርሶ አደሮች የገጠር መሬት በነፃ የማግኘት መብት አላቸው፡፡

ለ. ማንኛውም እድሜው 18 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆነና በክልሉ ውስጥ በግብርና ሥራ ሊተዳደር የሚፈልግ ማንኛውም ሰው በገጠር መሬት የመጠቀም መብቱ የተረጋገጠ ሆኖ እናትና አባታቸውን በሞት ወይም በሌላ ሁኔታ ያጡ ልጆች 18 ዓመት እስኪሞላቸው ድረስ በውርስ የሚያገኙት መሬት ከሌለ በህጋዊ ሞግዚቶቻቸው ወይም በወኪሎቻቸው አማካኝነት የገጠር መሬት የማግኘትና የመጠቀም መብት ይኖራቸዋል።

ሐ. በግብርና ስራ መሰማራት የሚፈልጉ የገጠር ሴቶች የገጠር መሬት የማግኘትና የመጠቀም መብት አላቸው።

መ. ማንኛውም አርሶ አደር በገጠር መሬት የመጠቀም መብት የጊዜ ገደብ የለውም።

ሠ. ኑሮአቸውን ከተማ ያደረጉ ነገር ግን ከግብርና ሥራ በሚገኝ ገቢ ብቻ የሚተዳደሩ ሰዎች የገጠር መሬት በነጻ የማግኘት መብት አላቸው፤ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል።

ረ. በገጠር መሬት ላይ በግለሰብ ደረጃ ለሚከናወኑ ባህላዊ የወርቅ ቁፋሮዎች ጥናትን መሠረት ባደረገ መልኩ የሚመለከታቸው የቀበሌ ወይም የንጥ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴዎች አማካኝነት እውቅና በመስጠት የገጠር መሬት በወል እንዲያገኙና እንዲጠቀሙበት ይደረጋል፤

## 6. THE RIGHT TO ACQUIRE and USE LAND

1. According to the land administration provisions:-

a. Any peasant and who wants to be engaged in agricultural sector shall have the right to acquire land freely.

b. Any person who is 18 years and above and residing in the region who wants to be engaged in agricultural activity shall have the right to use it and children under 18 where there is no land in heir, who lost their parents shall get and use the land through their guardian or their representative.

c. A woman who wants to engage in agricultural activities shall have the right to hold and use the land.

d. There is no time limit for any peasant with a right to use the rural land.

e. Those people (persons) who are residents in towns and deal with only agricultural activities for their livelihood shall have the right to acquire land freely. The detail shall be determined by regulations.

f. Traditional gold mining activities conducted by individual on rural land shall given recogntition based on studies by kebele and sub-kebele land administration and use committees and hence allowed to have and use communual land.

2. ማንኛውም በገጠር መሬት የመጠቀም መብት ያለው አርሶ አደር የቤተሰብ አባል ከቤተሰቡ በስጦታ ወይም በውርስ እንዲሁም በወረዳ ላይ በሚቋቋም የአካባቢ ጥበቃ መሬት አስትዳደር አጠቃቀም ባለስልጣን የገጠር መሬት በይዞታ ሊያገኝ ይችላል፣

3. የወል እና የጋራ የሆኑትን የገጠር መሬት ይዞታዎች መንግስት እንደአስፈላጊነቱ ወደ ግል ይዞታነት እንዲቀየሩ ሊያደርግ ይችላል፣

4. ለአርሶ አደሮች ቅድሚያ በመስጠት፣

**ሀ.** በግብርና ልማት ለሚሰማሩ ባለሃብቶች በፌዴራልና በክልል ደረጃ በወጡት የኢንቨስትመንት ፖሊሲዎችና ህጎች መሠረት እና በሚያቀርቡት የልማት ዓላማዎች ወይም ውጥኖች መሠረት አስፈላጊውን ሲያሟሉ የገጠር መሬትን የማግኘትና የመጠቀም መብት ይኖራቸዋል፣

**ለ.** መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተቋማት ከልማት አላማቸው ጋር እየታየ በገጠር መሬት የመጠቀም መብት ይኖራቸዋል፣

**ሐ.** በአንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 1 (ሀ) የተደነገገው ቢኖርም የግብርና መር ኢንዱስትሪውን ሽግግር ለማፋጠን ሲባል ኑሮአቸውን ከግብርና ውጭ በሌላ ሥራ የሚደጉሙ ሆነው ነገር ግን በግብርና ሥራ ተሰማርተው ውጤታማ የሆኑ እና መሆን የሚፈልጉ ሰዎች የአርሶ አደሩን ህልውና በማይጎዳ መልኩ የገጠር መሬትን ከባለስልጣኑ የወረዳ ተጠሪ መሥሪያ ቤት እና ከቀበሌና ከጎጥ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴዎች ጋር በሚደረግ የውል ስምምነት መሠረት የገጠር መሬት የሚያገኙበት ሥርዓት ይዘረጋል፤ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል።

5. የግል ባለሀብቶች የሚጠቀሙበትን መሬት ከመንግሥት በሊዝ ወይም ከማንኛውም የገጠር መሬት ባለይዞታ ጋር በሚደረግ ስምምነት በኪራይ የማግኘት መብት አላቸው፣

2. Any farmer who has the right to use the rural land can obtain rural land in holding it from the farmer by bequeath or donation or from the institution accountable to environment protection land administration authority yet to be established.

3. Rural lands hold communally or jointly may be changed to private holding by the government.

4. Giving priority to the farmers;

a. Investors who want to engage in agricultural sectors shall have the right to acquire and use the rural land based on investment policies and proclamation issued at Federal and Regional level and their development plans apply to it.

b. Governmental and non governmental organizations as well as social welfare institutions will have the right to use the rural land in accordance with their development plans.

C. pursuantt to sub article 1 a of article 13 of this proclamation, individuals engage other than agricultural means but insist to become effective by engaging to it, for acceleration of agriculture lead industry, by agreement to be made with the woreda responsible authority and kebeles rural land administration, a system that allows obtaining land shall be established. The detail shall be determined by the regulation.

5. Private investors shall have the right to acquire land, to use on, by rent from the government or from any other rural land holder based on the agreement to be made.

6. በክልሉ ውስጥ ሥራቸውን የሚያካሂዱ መንግሥታዊ መ/ቤቶችና ድርጅቶች፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የብዙሃን ማህበራትና የሃይማኖት ተቋማት ተግባራቸውን የሚያከናውኑት ለገንዘብ ትርፍ እስካልሆነ ድረስ የአርሶ አደሮችን መሬት የማግኘት መብት በማይፃረር ሁኔታ የሚቀጠሙበት መሬት በይዞታ የማግኘት መብት አላቸው፤

7. በአንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 6 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ሴቶች፣ ወላጅ አልባ ልጆች፣ አረጋውያን እና አቅመ ደካማ ቤተሰቦች እንዲሁም ሌሎች በተመሣሣይ ሁኔታ ውስጥ ያሉ ይዞታቸውን የሰው ሀይል በመቅጠር አሊያም በሌላ ስምምነት ሊጠቀሙ ይችላሉ፤

8. ከቀበሌ ውጭ በሆነ መንገድ በሚደረግ የመሬት የመጠቀም ጥያቄ ሁለቱ ቀበሌዎች በመስማማትና የሚመለከተው አካል ሲያረጋግጥ በመሬቱ የመጠቀም መብት ሊረጋገጥላቸው ይችላል፤ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል።

9. የመንግስት ሰራተኞች የገጠር መሬት በነጻ የማግኘት መብት አይኖራቸውም፤

### 7. መሬት በይዞታ የሚገኝባቸው ሁኔታዎችና የይዞታ ጣሪያ

1. በክልሉ ውስጥ ነዋሪ የሆነና በግብርና ሥራ የሚተዳደር ወይም በዚሁ ለመተዳደር የሚፈልግ ማንኛውም ሰው በሚከተለው አኳኋን የገጠር መሬት በይዞታ የማግኘት መብት አለው፤

ሀ. በመደበኛነት በሚኖርበት ወይም መኖር በሚፈልግበት ቀበሌመሬትን ከሚያስተዳድረው አካል በድልድል፤

ለ. ዝርዝሩ ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣ ደንብና የሚወሰን ሆኖ በማናቸውም የክልሉ አካባቢ በውርስ፣ በስጦታ ፣በሊዝ እና በኪራይ፤

6. Government offices and organizations, non governmental organizations, mass organizations and religious institutions that carried out activities in the region, all where it is not profit making, here the rent to acquire land they use on as long as that does not contravene the land holding of farmers.

7. Notwithstanding with the provison of sub-article 6 of article 5, orphans, elderlies, and the likes may allow to use their land by hiring or some other means.

8. The question to use land out side kebele may allow the right to use land shall be made by the agreement of the two kebeles and approval of the concerned authority details determined by regulation.

9. The civil servants shall not obtain rural land freely.

### 7. **Land aquairing means and holding size**

1. Any person who reside in the region and would like to engage in agricultural activity shall aquire land in one of the following procedure.

a. From land administrator of his kebele in which he permanent reside.

b. By bequeath, donation and rent the detail shall be determined by the regulation.

2. ለአንድ ሰው በይዞታ የሚሰጠው መሬት ጠቅላላ ስፋት ጣሪያ፣ መሬትን በሊዝ፣ በይዞታም ሆነ በኪራይ ለማግኘት ጥያቄ የሚቀርብበትም ሆነ ምላሽ የሚያገኝበት ሥርዓት ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም ወደፊት በሚወጣ ደንብ የሚደነገግ ይሆናል፤

**8.የመሬት ይዞታ ዋስትና ስለመስጠት**

1. የገጠር መሬት ባለይዞታነት መብት ያለው ማንኛውም አርሶ አደር ዕድሜ ልክ የሚቆይ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር በሚመለከተው አካል ይሰጠዋል፤
2. ማንኛውም የይዞታ መብቱን ያጣ አርሶ አደር ተሰጥቶት የነበረውን የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ለሚመለከተው ህጋዊ አካል የመመለስ ግዴታ አለበት፤
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ለሚመለከተው አካል የሚመለሰው መሬት፣ ይዞታ ለሌላቸው ወይም ላነሳቸው አርሶ አደሮች ይከፋፈላል፤
4. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የግል ይዞታ በሚከራይበት ጊዜ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር በአከራዩ እጅ ይቆያል፤
5. የይዞታ መብት የተሰጠው ማንኛውም አርሶ አደር የይዞታ መሬቱን የመጠቀም መብት የሚያረጋግጥ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር አግባብ ካለው አካል ይሰጠዋል፤ ዝርዝር አፈፃፀሙ በደንብ ይወሰናል፡፡
6. ባልና ሚስት በጋራ ይዞታቸው ላይ ጥምር የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያገኛሉ፡፡ በሌላ መልኩ በሃይማኖት ወይም በባህል የሚደረገው ጋብቻ አፈጻጸም ወደፊት በደንብ ይወሰናል፡፡
7. መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የግል ባለሀብቶችና ማህበራዊ ተቋማትም የይዞታ ባለቤትነት ደብተር ከአጠቃቀም እቅድ ጋር ይሰጣቸዋል፤
8. የባል ወይም የሚስት ወይም የሁለቱም አካባቢውን ለቆ መሄድ ወይም በሞት መለየት የቤተሰብ የመሬት ይዞታ የመጠቀም መብትን አያሳጣም፤

2. A system which determines maximum land holding size, submissions for aquering land through holding, rent and lease shall establish in the regulation.

**8. Giving warranty for holding**

1. Any peasant who possesses land holding right shall provide his life with land holding certificate by the authority.
2. Any peasant who lost holding right shall return holding certificate to the authority.
3. According to the provision of sub- article 2 of this article, the land to be return shall distribute to landless or scarce peasants.
4. According to sub-article 1 of article 20 of this proclamation, during rent, the holding certificate remains with the holders.
5. Any person who has land holding right shall provide with land holding certificate that approve use right of the holding. The detail shall be determined by the regulation.
6. Spouses shall obtain land holding certificate jointly from their common holding. But marriage done by religious or cultural shall be determined by the regulation.
7. Theholding certificate with land use plan shall provide to government, non-government organizations, private and civic institutions.
8. Either spouses or both parents leave the area or by death shall not deny using right of the family.

9. የይዞታ መብት ለውጥ በሚደረግበት ጊዜ በአንፃሩም ይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እድሳትም ይደረጋል፤

10. ማንኛውም ሰው በሕግ ያልተሰጠውን መሬት ሲጠቀም ከተገኘ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ የያዘውን መሬት እንዲያጣ ይደረግና በሕግ ይጠየቃል፤ ዝርዝር አፈፃፀሙ በደንብ ይወሰናል፡;

9. **ስለመሬት ሽግሽግ እና ክፍፍል**

1. የመሬት ባለይዞታዎች በህይወት የሌሉና ወራሽ የሌላቸው ከሆኑ ወይም ባለይዞታዎቹ በሰፈራ ወይም በፍላጎታቸው በክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደር ህግ ከተወሰነው ጊዜ በላይ ከአካባቢው ለቀው የቆዩ ከሆነ ወይም ያልተያዙ ኪስ መሬቶች በአካባቢው ለሚኖሩት መሬት አልባ ለሆኑ ወይም መሬት ላነሳቸው አርሶ አደሮች መሬት በክፍፍል እንዲሰጥ ይደረጋል፤ የአሰጣጥ ቅደም ተከተሉ ዝርዝር በደንብ ይወሰናል፡፡

2. የመሬት ሽግሽግ በህብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት የሚኖረው ከሆነና ከሰማኒያ በመቶ እና ከዚያ በላይ የሚሆኑትና በአንድ ቀበሌ ውስጥ የሚገኙት ባለይዞታዎች የመሬት ክፍፍል እንዲካሄድ በጽሁፍ ወስነው ጥያቄውን ለባለሥልጣኑ ካቀረቡ ይህንኑ ውሣኔ ለማስፈፀም በሚወጣ ደንብ መሠረት ጥያቄው በቀረበበት የይዞታ ሽፋን የመሬት ሽግሽግ ሊካሄድ ይችላል፡፡ አለበለዚያ የመሬት ሽግሽግ ፈፅሞ አይካሄድም፤ ተፈፃሚነቱም በሁሉም ባለይዞታዎች ላይ ይሆናል፡፡

9. When there is a change in holding right, the land holding certificate shall change.

10. Any person found using land which is not provided by law shall loss the land and held accountable by law. The detail shall be determined by regulation.

**9. Land Re-distribution and Distribution**

1. If a land left with no heir or because of settlement left the area for more than the time set by the law and from unoccupied land, it will distribute to landless or land scarce peasants. The sequence of the provision shall be decided by the regulation.

2. Where the land holders residing in one kebele and where not less than 80 per cent of the reqest the Authority in writing for land distribution, the land redistribution may be carried out in accordance with a regulation to be issued to implement this decision on the land where the question was submitted. Its application shall be on all holders.

3. የገጠር መሬት ሽግሽግ ማካሄድ አማራጭ የሌለው ሆኖ ሲገኝ ከአነስተኛ የይዞታ መጠን በታች በማይሆንና የምግብ ዋስትናን በማይጎዳ እንዲሁም የተፈጥሮ ሃብት መመናመንን በማያስከትል መልኩ ተግባራዊ መሆን አለበት፤
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ በክልሉ ውስጥ በመስኖ የሚለማ መሬት ካልሆነ በስተቀር የአርሶ አደሩ የመሬት ይዞታ አይሸጋሸግም፤
5. በሕዝብ ጥያቄ መሠረት የመሬት ሽግሽግ በሚካሄድበት ጊዜ መሬት ተቀንሶ የሚወሰድበት ባለይዞታ የመሬት መበጣጠስን የሚያስከትል እስካልሆነ ድረስ የመረጠውን የመሬቱን ክፍል የማስቀረትና በመሬቱ ላይ ላለማው አንስቶ ሊወስደው ለማይችል ንብረት፤ መሬቱ ከሚሰጠው ሰው ወይም ሽግሽጉ እንዲካሄድ ከሚፈልገው አካል ተመጣጣኝ ካሣ በቅድሚያ የማግኘት መብቱ የተጠበቀ ነው፤ ዝርዝሩ በደንብና ይወሰናል፡፡
6. ባልና ሚስት በፍቺ ወቅት ቀድሞ በጋራ ይጠቀሙበት የነበረዉን የይዞታ መጠን ፍትሀዊ በሆነ መልኩ የተለያዩ ታሳቢዎችን ግምት ዉስጥ በማስገባት በሚመለከተዉ የህግ አግባብ እንዲከፋፈሉ ይደረጋል፡፡

### 10. የመሬት አሰጣጥ ሥርዓትና የሚሰጠው መሬት ዝቅተኛ መጠን

1. የመሬት አሰጣጥ ሥርዓት እንደጠያቂዎች የመሬት ፍላጐት በሕዝብ ተሳትፎ በሚወሰነው ቅደም ተከተል መሠረት መሬት በይዞታ የማግኘት መብት ላላቸው አመልካቾች ሁሉ ያለአድልዖ እንዲፈጸም ይደረጋል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም ሊሰጥ የሚችለው የመሬት መጠን እኩል የመሬት ችግር ላለባቸው ጠያቂዎች የማይዳረስ ከሆነ እንደ ቅደም ተከተላቸው ለወላጅ አልባ ሕፃናት፣ ለአካል ጉዳተኞች፣ ለአቅመ ደካሞች፣ ለሴቶችና ለአዲስ ጐጆ ወጪዎች ቅድሚያ እንዲሰጥ ይደረጋል፤

3. If the decision passed to go ahead with land re-distribution, it should not be below the minimum holding size and should not affect the food security and avoid damge on the natural resource.
4. Notwithstanding provisions of sub- Article 2 of this Article, the peasant land holding shall not be re-distributed.
5. When the land distribution or allotment is carried out based on request of the people, the land holder whose land is to be decreased and taken shall, where it does not bring land division in to pieces, have a right to get the land he has chosen and get compensation for an asset he produced and could not pick up. The detail shall be determined by a regulation.
6. When a divorce made between spouses, they will divide their holding in equitable manner by taking in to account different consideration with appropriate law.

### 10. The procedure of land provision and minimum area of land to be provided

1. The provision of land shall be made to all applicants, impartially, having a right to aquire land in holding based on petitioners interst and a sequence to be determined by the participation of the people.
2. Notwithstanding provision of sub- article 1 of this article, where the land to be distributed is not available to all petitioners with equal magnitude of land holding problem it shall priorly be caused to be given to orphan children, disabled women and yongsters who join the new life of independence consequetively.

3. የሚሰጠው መሬት መጠን በሚወሰንበት ጊዜ የመሬቱ ለምነት ደረጃና ሌሎች ታሳቢዎች ግምት ውስጥ እንዲገቡ ይደረጋል። ዝርዝር አፈጻጸሙ በደንብ ይወሰናል፤

4. ለአንድ ሰው የሚሰጠው በዝናብ ወይም በመስኖ የሚለማ የአንድ ማሳ አነስተኛ መጠንም ይህንን አዋጅ ተከትሎ በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፤

5. ለግጦሽ፣ ለደን ልማትና ለመሳሰሉት ተግባራት የገጠር መሬት ሲውል አመቺ በሆነው የይዞታ አይነት (በወልም ሆነ በተናጠል) የይዞታ መብት የሚረጋገጥ ሲሆን በይዞታነት የሚሰጥ አነስተኛ የይዞታ መጠንም ይህንን አዋጅ ተከትሎ በሚወጣ ደንብ ይወሰናል ፤

11. የይዞታ ዓይነቶች

በክልሉ የሚገኝ የገጠር መሬት በግል፣ በጋራ፣ በወል እና በመንግሥት ሊያዝ ይችላል፤

12. ስለይዞታና የመጠቀም መብቶች መከበር

1. የማንኛውም ሰው ይዞታ በሕግ የተጠበቀ ነው። በመሆኑም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 2 ወይም አንቀጽ 33 እንደተደነገገው በሕዝብ ውሣኔ መሠረት በሚደረግ ሽግሽግ ወይም መሬቱን ለሕዝብ አገልግሎት ለማዋል ካልሆነ በስተቀር ማንም ሰው የያዘውን መሬት ከፈቃዱ ውጭ አይነጠቅም፤

2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 13 እና 22 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ባለይዞታ በገጠር መሬት የመጠቀም መብቱን እንዲያጣ አይደረግም፤

3. During the time of deciding the area of land to be distributed, the fertility of land and grade, and other assumptionsto be stated in the regulation shall be considered.

4. The minimum area of plot of land, to be provided to one person and cultivable by rain or irrigation shall, be determined by a regulation to be issued following this proclamation.

5. Land shall be hold commonly or communally for the activities like forest, grazing and the likes and the holding size shall determine by the regulation to be issued follwing this proclamati

11. **Types of holdings**

The rural land in the region may be held individually, grouplly, communally and the government.

**12. Respection of holding and using Rights**

1. The holding of any person is respected by law. Therefore, pursuant to provision of sub- article 2 of article 9 or article 33 of this proclamation, no person shall be expropriated from his holding with out the consent, unless it is done by re- distribution according to the decision of people or for the purpose of public interest.

2. Notwithstanding with the provision stated under article 13 and 22 of this proclamation, any person provided with holding right shall not be deprived from the right to use.

13. የይዞታ መብት የሚታጣባቸው ሁኔታዎች

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የተደነገገው ቢኖርም በመሬት የመጠቀም መብት ያለው ማንኛውም ባለይዞታ በሚከተሉት ምክንያቶች በመሬት ይዞታ የመጠቀም መብቱን እንዲያጣ ሊወሰን ይችላል፤

ሀ. ዝርዝሩ በደንብ የሚወሰን ሆኖ ከግብርና ውጭ በሆነ ሥራ ላይየተሰማራና ገቢ የሚያገኝበት ቋሚ መተዳደሪያ ያለው ማንኛውም ሰው የገጠር መሬትን በነፃ ሊያገኝ አይችልም፤

ለ. ያለበት ቦታ ሳይታወቅና መሬቱን ሳያከራይ ወይም የሚያስተዳድርለት ሰው ሳይመድብ በተከታታይ ከሶስት ዓመታት በላይ ከመኖሪያ ቦታው የጠፋ እንደሆነና ስለመጥፋቱም አግባብ ያለው የህግ አካል ሲያሳውቅ፣

ሐ. ያለበቂ ምክንያት በተከታታይ ከሶስት ዓመታት በላይ ወይም በመስኖ የሚለማ መሬት ሲሆን ከሁለት ዓመት በላይ መሬቱን በጥቅም ላይ ያላዋለ እንደሆነ፣

መ. ዝርዝሩ በደንብ የሚወሰን ሆኖ የይዞታ መሬቱን በእንክብካቤ ባለመያዙ ምክንያት በመሬቱ ላይ ከባድ ጉዳት የደረሰ እንደሆነ፣

ሠ. የመሬት ይዞታ መብቱን በራሱ ፈቃድ መተውን ለሚመለከተው አካል ያሣወቀ አንደሆነ፣

2. የጠፋው ባለይዞታ የትዳር ጓደኛ ወይም አካለ መጠን ያልደረሰና አብሮ የሚኖር መሬት የሌለው ልጅ ካለው ወይም የጠፋው ባልተጠበቀ ድንገተኛ ሁኔታ ለመሆኑ የማያጠራጥር መረጃ ከተገኘ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ ቁጥር ለ ና ሐ ሥር የሰፈረው ድንጋጌ ተፈፃሚ አይሆንም፤

13. **Condition depriving land holding**

1. Notwithstanding provision under sub-article 1 of article 12 of this proclamation, any holder having a right over using the land, it may be decided to be deprived from the right of using the land by the following reasons;

a. The detail to be determined in regulation, where he is engaged in non-farming activity and earns for his livelihood thereto;

b. Where he disappears from his residence for 3 consecutive years without notifying his where abouts and not renting his land or without assigning a representative to administer his land

c. Where he follows his land for 3 consecutive years and above or 2 years and above where the land is cultivable in irrigation

d. The detail to be determined by regulation where gross damage occurs over his land due to mismanagement.

e. Where he notifies to the concerned body that he has withdrawn from his holding right.

2. Where a disappear land holder has a spouse or a minor who lives with him and has no land or where there is a doubtful information that his disappearance is due to unexpected accidental situation, the provision stated under sub-article 1b and c and this article shall not be applicable.

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ አንድ ፊደል ተራ ቁጥር ለ ና ሐ ድጋገዎች መሰረት ባለይዞታዉ ለጊዘዉ የጠፋ ወይም አስተዳዳሪ ያልተመደበለት ማናቸዉም የገጠር መሬት እንደ ሁነታዉ በተከታታይ ሁለት አመታት ወይም በመስኖ ለሚለማ ይዞታ ለተጠቀሰዉ ጊዜ ያህል ጥቅም ላይ አለመዋሉ የተረጋገጠ እንደሆነ መሬት ለሌላቸው ወይም አነስተኛ መሬት ላላቸዉ አመልካቾች በጊዜያዊነት ጥቅም ላይ እንድዉል ሊሰጥ ይችላል፡፡ዝርዝር አፈጻጸሙ በደንብ ይወሰናል፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሀ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ መብቱን ያጣ ማንኛውም ሰው በመሬቱ ላይ ላለማው ቋሚ ንብረት ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣ ደንብ በሚደነግገው ህግ የሚወሰን ሆኖ ተገቢውን ካሣ የማግኘት መብት ይኖረዋል፤

### 14. መሬትን በጥናትና በእቅድ ስለመጠቀም

1. የክልሉ የመሬት አጠቃቀም እቅድ መዘጋጀት አለበት፡፡ የመሬት አጠቃቀም እቅድ አዘገጃጀት አቅምን ያገናዘበና ደረጃ በደረጃ የሚፈፀም ሲሆን መሬት ለአንድ ለተወሰነ የአጠቃቀም ዓይነት እንዲውል ይደረጋል፤
2. ማናቸውም የገጠር መሬት የአጠቃቀም ዕቅድ አቅም በፈቀደ መጠን በጥናትና በመረጃ በተደገፈ መልኩ ጉዳዩ በሚመለከተው አካል በኩል ይወጣለታል፤
3. የገጠር መሬት የአጠቃቀም ዕቅድ የውሃ ተፋሰስን መሠረት አድርጐ የመሬት አጠቃቀምን፣ የአፈር አይነትን፣ የአየር ጠባይን፣ የእፅዋት ሽፋንን እንዲሁም ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ወዘተ… ሁኔታዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት መዘጋጀት አለበት፤
4. ማንኛውም የመሬት ተጠቃሚ በሚወጣው የገጠር መሬት አጠቃቀም ዕቅድ መሠረት ብቻ እንዲገለገል ይደረጋል፤

3. Pursuant to provision of sub-article 1b and c of this article, where the land holder disappears or the land administrator is not assigned, ascertaining that of fallow for 2 consecutive years and left uncultivated in irrigation for 1 years, may temporarily be given to those who do not have land or small land holding up on their petition. The detail shall be determined by regulation.

4. Any person who is deprived from his land holding right pursuant to sub-article 1,a of this article, shall have a right to get compensation for permanent he had developed on the land and in accordance with the regulation to be issued to implement this proclamation.

### 14. UTILIZATION OF LAND ON PLAN AND STUDY

1. Land use plan of the region shall be prepared. The preparations of the plan need to consider the existing capacity and need where the land shall be made for specific utilization.
2. Any rural land use plan, as much as possible, based on study and evidence shall be prepared by competent body.
3. Rural land use plan shall base itself on watershed and its preparation shall consider like, land use, soil type,weather condition, vegetation/crop/ cverage as well as socio-economic and political situations.
4. Any land user shall be made use only in accordance with land use plan to be issued thereof.

5. ማንኛውም መሬት ለአንድ አገልግሎት እንዲውል ሲደረግ፦

ሀ. የተሻለ የኢኮኖሚ ጠቀሜታ የሚሰጥ መሆኑ፣

ለ. በአካባቢ ላይ የሚያስከትለው ተፅዕኖ አለመኖሩ ወይም ተጽዕኖ አነስተኛ መሆኑ፣

ሐ. አገልግሎቱ በአካባቢው ተጠቃሚዎች ዘንድ ተቀባይነት ያለው መሆኑ ሲረጋገጥ መሆን ይኖርበታል።

6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አግባብ ካለው አካል በጽሁፍ ተዘጋጅቶ የተሰጠ የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ የሌለ እንደሆነ ማንኛውም የመሬት ተጠቃሚ መሬቱን ለቤት መሥሪያ፣ ለእርሻ፣ ለአንስሣት እርባታ፣ ለደን ልማት ወይም ከእነዚሁ ጋር ግንኙነት ላላቸው ሌሎች ተግባራት ሊገለገልበት ይችላል፤

7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 የተደነገገው ቢኖርም ማንኛውም ተጠቃሚ መሬቱን በሕግ ለተከለከለ ተግባር ሊያውለው አይችልም፤ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል።

8. ወቅታዊ የመሬት አጠቃቀም ለውጥ የሚካሄደው በጥናት በተደገፈ መረጃ ላይ ዕቅድ ሲወጣና በዚህ እቅድ ተመስርቶ ጥቅም ላይ እንዲውል ሲደረግ ብቻ ነው፤

9. የመሬት አጠቃቀም ለውጥ የሚያስከትለው አሉታዊና አዎንታዊ ተፅዕኖ በመገምገም የመፍትሄ አቅጣጫ ለመተለም የሚያስችል የጥናትና ምርምር ተግባር መካሄድ ይኖርበታል፤

10. የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ዕቅድ በየጊዜውና በየወቅቱ በየወቅቱ መረጃን መሠረት በማድረግ በሳይንሳዊ መንገድ እየተጠና ለተሻለ አገልግሎት እንዲውል ለማድረግ ባለስልጣን መሥሪያ ቤቱ የሚመለከታቸውን አካላት የማስተባበርና የማቀናጀት ኃላፊነት አለበት፤

5. Where any land is made for a given service.

a. whether its provision is for better economic benefit

b. The absence or existence of the impact it has on the environment.

c. The acceptability of the service by beneficiaries shall be ascertained.

6. Without prejudice to provision of sub-article 4 of this article, where there is no land use plan prepared in writing by pertinent body, any land user may use his land for house construction, animal husbandry, forestry development uses.

7. Notwithstanding the provision stated under sub-article 6 of this article, any land user cannot use his land for legally prohibited utility. The details shall be determined by the regulation.

8. Timely land use change shall be conducted only when a plan developed based on study and evidence and utilization is made accordingly.

9. Research and study for evaluation of the positive and negative impact caused by the change of land utilization enabling to predict the direction of the solution shall be conducted.

10. Strategic and operational land use shall be applicable based on study through scientifical means for its better service, shall be made by the Authority in integrating and coordinatig of competent bodies.

11. የተሻለ የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ ሥርዓትን ለማስፈን የሚያስችል የመንደር ማሰባሰብ፣ የሰፈራ ፕሮግራምና ሌሎች ማኀበራዊ አገልግሎቶች የሚስፋፉበትን ስልት ባለስልጣን መሥሪያ ቤቱ የሚመለከታቸው አካላትን በማቀናጀት የመሬት አጠቃቀሙን ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ በማቀድና የገጠር ቦታዎችን በመለየት የሚያስፈልገውን የመሬት ስፋት ደረጃ እንዲወጣለትና አሰቀድሞ እንዲዘጋጅ በማድረግ በተፈጥሮ ሃብት ላይ ሊደርስ የሚችለውን ጫና መቀነስ አለበት፤

12. የመሬት አጠቃቀም ዕቅድን መሠረት ያላደረገና በጥናት ላይ ያልተመሰረተ በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት የሌለው በገጠር መሬት ላይ የሚካሄድ ህገ ወጥ የሆነ ሰፈራና የመሬት ወረራ እንዳይካሄድ የሚመለከታቸው አካላት ሁሉ በየስልጣን እርከኖቻቸው በቅንጅትም ሆነ በተናጠል የመከላከል ሃላፊነት አለባቸው፤

13. የመንግስት፣ የግልና ሌሎች የምርምር ተቋሞች በዘርፉ ጥናትና ምርምር ለማካሄድ እንዲችሉ ባለስልጣን መሥሪያ ቤቱ ሁኔታዎችን የማመቻቸትና ለተጠቃሚው ህብረተሰብ በወቅቱ እንዲደርሱ ማድረግ አለበት፤

14. በክልሉ ቆላማ እና ከፊል ቆላማ አካባቢዎች በብዛት የሚዘወተረውን የተዘዋዋሪ እርሻ የአስተራረስ ዘይቤ ጠቀሜታው ጎልቶ በሚታይባቸውና ምቹ ሁኔታዎች በሚገኙባቸው አካባቢዎች የአጠቃቀም እቅዱን በመንደፍ ጥናቱን ያገናዘበ የይዞታ ስፋት ተወስኖ በይዞታቸው ሥር ባለ መሬት ላይ ብቻ እየተዘዋወሩ እንዲጠቀሙ መደረግ አለበት፤ ዝርዝር አፈጻጸሙ በደንብ ይወሰናል፡፡

**15. በመስኖ ስለሚለሙ መሬቶች**

1. የመስኖ መሬትንና የውኃ ሃብትን በአግባቡ ለመጠቀም የመስኖ መሬትን ማከፋፈልና ማሸጋሸግ በሚከተለው አኳኋን ይከናወናል፤

ሀ. የአንድ አባወራ ከፍተኛውና ዝቅተኛው የይዞታ መጠን በሚለማው ይዞታ መጠን ስፋት፣ በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና የተለያዩ ምክንያቶችን ከግምት ውስጥ ያስገባ ሆኖ በማህበረሰቡ ተሳትፎ መሠረት የሚወሰን ይሆናል፤

11. The settlement that allows better land use plan shall be designed by the Authority and has integrate competent bodies in planning land use through scientifical means, identification of rural area, in issuing the grade of the land which shall reduce the impact on natural resource degradation.

12. Illegal settlement or invasion of land which is not based on study and land use plan shall be avoided by concerned body in their level of Athority individually or jointly.

13. The Authority shall creat conducive conditions for government, private and other research institutions in duing land use studies.

14. In the region, arid and semiarid areas where shifting cultivation is predominant where the practice is higher and the situation is conducive in the area, the utilization plan will be conducted and holding size study and shifting shall be utilized within the holdings. The detail will be determined by the regulation.

**15. IRRIGATION DEVELOPMENT**

1. In order to properly utilize irrigation land and water resource potentials, irrigation land shall be distributed and redistributed as follows;

a. The highest and the minimum holding size of a household shall be determined based on the area need to be productive, social economy need to be considered; which is to be determined by the participation of the community.

ለ. የመሬት ይዞታቸው በመስኖ ሊለማ በሚችልበት መሬት ስር ለወደቀ ባለይዞታቸው ቅድሚያ በመስጠት ቀሪውን የመስኖ መሬት በቅርብ ርቀት ለሚኖሩ አርሶ አደሮች የሚከፋፈል ይሆናል፤

ሐ. ይዞታው በመስኖ ሊለማ በሚችል መሬት ሥር ውሎ ይዞታው ለሌሎች የተከፋፈለበት ማንኛውም አርሶ አደር በዝናብ ሊለማ የሚችል ተመጣጣኝ መሬት በለውጥ ይሰጠዋል፤

መ. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሐ የተደነገገው እንደጠጠበቀ ሆኖ በመሬቱ ፊዚካላዊ አቀማመጥ አስገዳጅነት ይዞታው በመስኖ ግንባታ ስር የዋለበት ማንኛውም አርሶ አደር ይዞታውን የመፍቀድ ግዴታ አለበት። ሆኖም በይዞታው ላይ ለሚገኝ ንብረቱ ተጠቃሚው ማህበረሰብ ካሣ እንዲከፍለው የመጠየቅ መብት አለው፤

ሠ. ማንኛውም የመስኖ መሬት ተጠቃሚ በአግባቡና ሙሉ በሙሉ መሬትን ጥቅም ላይ የማዋል ግዴታ አለበት፤

2. ባህላዊ የመስኖ አጠቃቀም በአካባቢው ህብረተሰብ ባህላዊ ደንብና በሚመለከታቸው የሙያ መ/ቤቶች ምክር ተደግፍ እንዲካሄድ ይደረጋል;

3. የሚመለከታቸው የሙያ መ/ቤቶች የሚያወጧቸውን መመዘኛዎች ተፈፃሚ የማድረጉ ግዴታ እንደተጠ በቀ ሆኖ ማናቸውም ዘመናዊ የመስኖ ልማት ሥራ ከመካሄዱ አስቀድሞ ዝርዝር የዲዛይን ጥናቶች መደረጋቸውን ለሚገነባው ግድብ አስፈላጊው የተፋሰስ ሥራ መከናወኑና በግድቡ ግንባታ ምክንያት ተቆፍሮ የሚወጣው አፈርና ድንጋይ በህብረተሰቡ ላይ ጉዳት የማያስከትል መሆኑን ማረጋገጥ አስፈላጊ ይሆናል፤

b. Holders who come under irrigation in holding shall be given priority and the remaining land shall be allowed for the peasants who live near to the land.

c. Any peasant whose land holding falls under irrigation development and redistributed to others, shall be compensated by rainfed land.

d. Notwithstanding of the provision stated under sub-Article 1, c of this Article, any peasant who’s holding due to its physical nature falls under irrigation construction shall have the obligation to allow the land. However he has a right to ask for compensation from the beneficiary.

e. Any irrigation land user shall be obliged to use the land fairly and properly.

2. The traditional irrigation usage shall be carried out supported by community cultural rules and counseling and pertinent professional offices.

3. Without prejudice to the obligation to apply the requirements to be issued by professional offices, before any modern irrigation activities carried out it shall be necessary to ensure the undertakings of the detailed design works for the dam to be constructed, conducting of the catchment works, and the non-damaging of the soil and stone dam during the dam construction on public.

4. የመስኖ ልማት ሲካሄድ ለአካባቢው ህብረተሰብ የበሽታ ምንጭ እንዳይሆንና እንዲሁም የአካባቢ ጉዳትን ማለትም የአፈር መሸርሸርን፣ የውሃ ብክነትና ብክለትን፣ የታችኛው ተፋሰስ ተጠቃሚዎችን፣ የመሬት ጨዋማነትና የመሳሰሉትን እንዳያስከትል ተጠቃሚዎች ከሚመለከታቸው የሙያ መ/ቤቶች በምክር ተደግፈው የመከላከል ግዴታ አለባቸው፤

5. በመሬታቸው ላይ የመስኖ መሠረተ ልማት ግንባታና የውሃ ግድብ የተሰራባቸው ባለይዞታዎች በመስኖ የሚለማው መሬት ውስጥ ምትክ ቦታና በመሬቱ ላይ ላለሙት ንብረት በግድቡ ተጠቃሚዎች የሚተካ ተገቢው ካሣ በቅድሚያ ይከፈላቸዋል፤

6. የመስኖ ተጠቃሚው ህብረተሰብ ለመስኖ መሠረት ልማት አውታሮችና ለተፋሰሱ ከመንግሥት ጋር በመተባበር አስፈላጊውን ጥንቃቄና ጥበቃ የማድረግ ግዴታ አለበት፤

7. ማንኛውም የመስኖ ተጠቃሚ አርሶ አደር ቢያንስ በዓመት ሁለት ጊዜ ዓመታዊ ሰብል የማምረት ግዴታ አለበት። አጥጋቢ ባልሆነ ምክንያት ይህንን የማይተገብር ባለይዞታ የመጠቀም መብቱን ከዛም ባለፈ ደግሞ የይዞታ መብቱን ሊያጣ ይችላል፤ ዝርዝር አፈጻጸሙ በደንብ ይወሰናል።

4. Any land user shall be duty bound with the advice of professional offices in preventing unnecessary consequences in connection with irrigation development such as not to be causes of disease, soil erosion, pollution, loss of water and salinity to lower watershed user, salinity and other which cause damage to the environment.

5. The land holders, on whose land the irrigation infrastructure and water dam are built shall be provided with irrigable land in substitution and be paid compensation priory without it may be substituted by the would be dam users for assets owned in their land.

6. The society using irrigation shall have the obligation to take care and in collaboration with government for irrigation infrastructure.

7. Any irrigation beneficiary and peasant shall have the obligation to cultivate annual crops at least twice a year; failing to do without any sufficient, he might lose using right and holding right, the detail shall be determined by regulation.

## ክፍል ሦስት
## የመሬት ይዞታና የመጠቀም መብቶችን ስለማስተላለፍና ስለግዴታዎች

### 16. የመሬት ይዞታ መብትን ስለማስተላለፍ

1. የገጠር መሬት ይዞታ የተሰጠው አርሶ አደር የይዞታ መብቱን በዚህ አንቀጽ ሥር በተደነገገው አኳኋን በውርስ፣ በስጦታ፣ በኪራይ ማስተላለፍ ይችላል፤ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል።
2. የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር የተሰጠው አርሶ አደር የምግብ ዋስትናውን በማይጎዳ እና የመሬት ይዞታውን በማያፈናቅል መልኩ ለሌላ አርሶ አደር ወይም ባለሃብት እንደየአካባቢው ተጨባጭሁኔታ በጥናት ላይ ተመስርቶ በሚወሰን አኳኋን ለተፈላጊው ልማት በቂ የሆነ የይዞታ ስፋት ማከራየት ይችላል፤ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል።
3. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 18 ንዑስ አንቀጽ 4 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የሠፈረው መብት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 6 መሠረት መሬት በይዞታ ለተሰጣቸው ድርጅቶች ተፈፃሚ አይሆንም፤
4. ማንኛውም በመሬት የመጠቀም መብት የተሰጠው ህጋዊ አካል በመሬቱ ላይ በጉልበቱና በገንዘቡ ያፈራውን ሃብት ለሌላ ህጋዊ አካል የመሸጥ፣ የማከራየት፣ የማውረስና በዕዳ ዋስትና የማስያዝ መብት አለው፤

### 17. የመሬት ይዞታና የመጠቀም መብትን በውርስ ስለማስተላለፍ

1. በዚህ አዋጅ መሠረት የገጠር መሬት ባለይዞታ የሆነ ማንኛውም ሰው የይዞታም ሆነ የመጠቀም መብቱን በግብርና ሥራ ለሚተዳደር ወይም በዚሁ ለመተዳደር ለሚፈልግ የቤተሰብ አባል አግባብ ባለው ህግ መሠረት በውርስ ማስተላለፍ ይችላል፤

## PART THREE
## TRANSFERING LAND HOLDING AND USING RIGHT AND OBLIGATIONS.

### 16. Transfering Holding Right

1. Any peasant provided with rural land shall transfer holding right by beaqueth, gift and rent as stipulated here in under; the detailed detemined by the regulation.
2. Any peasant provided with the land holding certificate with out affecting his food security based on the local situation determined by the study shall made a rent for proposed development activity. The detail determined by the regulation.
3. Notwithstanding with the provision stated under sub-article 4 of article 18 of the proclamation which stated under sub-article 6 of article 6 of the proclamation shall not be applicable for land holding institutions.
4. Any body that has the rigtht to use land shall have the right to sell, rent and mortgage the property developed on the land.

### 17. TRANSFERRING POSSESSION RIGHT IN BEQUEATH

1. Any person who is made of rural land holder in accordance with this proclamation may transfer the holding and using right in will to any farmer engaged or like to engage in agriculture.

2. የሚደረገው የመሬት ውርስ የእርሻ ማሳን መበጣጠስ የሚያስከትልና ዝቅተኛ የማሳ መጠን በታች ከሆነ ወራሾች መሬቱን በጋራ ወይም ከመከፋፈል ውጪ በሌላ በተስማሙበት አማራጭ ሊጠቀሙበት ይችላሉ፤
3. ወራሽ ያልተገኘለት መሬት፣ ይዞታ ለሌላቸው ወይም ላነሳቸው አርሶ አደሮች ይከፋፈላል፤

4. ለውርስ ዓላማ ሲባል የገጠር ኑሮአቸውን ለመደጐም ዝቅተኛ ገቢ የሚያስገኝ ሥራ እየሠሩ በከተማ የሚቀመጡ ሰዎች እንደ አርሶ አደር ይቆጠራሉ፤

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የተደነገገው የይዞታና የመጠቀም መብትን በኑዛዜ የማስተላለፍ ወይም የማውረሱ መብት አካለ መጠን ያልደረሰውን የተናዛዡን ልጅ ወይም ቤተሰብ ከወራሽነት መብት ከህግ ውጭ የሚነቅል ወይም የተናዛዡን የትዳር ጓደኛ የሚጐዳ ሆኖ ከተገኘ በሕግ ፊት የሚፀና አይሆንም፡፡ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፤
6. ማንኛውም የመሬት ባለይዞታ የይዞታ መብቱን በቋሚነት በግብርና ሥራ ለመተዳደር ለሚፈልግ የቤተሰብ አባል ወይም ለማንኛውም አርሶ አደር በኑዛዜ ማስተላለፍ ይችላል፤ እንዲሁም ደግሞ ለተወሰነ ጊዜ የመጠቀም መብቱን በኑዛዜ ከአንድ በላይ ለሆኑ ሰዎች ሊያስተላለፍ ይችላል፤

7. አንድ የመሬት ባለይዞታ የይዞታና የመጠቀም መብቱን በተመለከተ ሳይናዘዝ የሞተ እንደሆነ መብቱ በግብርና ሥራ ለሚተዳደር ወይም በዚሁ መተዳደር ለሚፈልግ የቤተሰብ አባል ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣ ደንብ በሚደነገገው ቅደም ተከተል መሠረት ይተላለፋል፤

2. Whenever inheritance may cause parcelization of farm plots beyond the determined minimum specified, the inheritors shall either jointly use the land or by whatever other means other than splitting the plot.

3. A land for which heir is not found, shall be distributed to the landless or to the land scarce peasants.

4. Persons residing in towns and engaged in small income earning activities to support their livelihood shall be considered farmers for the aim of succession.

5. Transferring in will or in inheriting the holding and use right, stipulated under sub-article 1 shall not be valid where it disinherit the minor child of the testator or the family of same from inheritance right or harms his spouse. The detail shall be determined by regulation.
6. Any land holder may, in will transfer his holding right and for limited period of time his use right to more than one person.
7. Where a land holder dies without making a will, as to the holding and use right of the land, the right shall be transferred to his child or families engaged or like to be engaged in agricultural works, consecutively, in accordance with the provisions of the regulations to be issued to implement this proclamation.

8. አንድ ሰው ሳይናዘዝ በሞተበት ወቅት በክልሉ ውስጥ የሚኖርና በግብርና ሥራ የሚተዳደር ወይም ለመተዳደር የሚፈልግ ልጅ ወይም ቤተሰብ የሌለው እንደሆነ ወላጆቹ በክልሉ ውስጥ ነዋሪዎች ሆነው በግብርና ሥራ የሚተዳደሩ ወይም ለመተዳደር የሚፈልጉ ከሆኑና አስቀድሞ ያላቸው የገጠር መሬት ይዞታ መጠን ከከፍተኛው የይዞታ መጠን በታች መሆኑ ከታወቀ የመሬት ይዞታውን የመውረስ መብት ይኖራቸዋል፤

9. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 8 የተደነገገው የወራሾች መብት በሕይወት ያለው የትዳር ጓደኛ በመሬቱ ላይ እየተጠቀመ ከመቆየቱ የሚከለክለው አይሆንም፡፡ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፤

10. ከአንድ በላይ የሆኑ ወራሾች በውርስ ያገኙትን መሬት በሚከፋፈሉበት ጊዜ የእያንዳንዳቸው ድርሻ በደንቡ ከተወሰነው የአንድ ማሣ አነስተኛ መጠን በታች የሆነ እንደሆን መሬቱን በጋራ መጠቀም እንጂ መከፋፈል አይችሉም፤

11. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1፣ 5 ወይም 6 ድንጋጌዎች መሠረት ወራሽ ያልተገኘለት የገጠር መሬት በባዶ ቦታነት ተመዝግቦ ለአዲስ አመልካቾች ይከፋፈላል፤

8. Where a man or women dies without making a will and he does not have a child residing in the region engaged or like to be engaged in agricultural works, or where he does not family, his parents who are residents of the region engaged or like to be engaged in agricultural works and priory land holding.

9. The right of heirs provided under sub-article 8 of this article shall not have prohibition to stay using the land where the alive spouse continues to reside in that kebele it remains for his lifetime.

10. Where more than one heir shares the inherited land, and where the share of each share is less than the minimum plot of land holding determined by regulation, they shall not partition the land other than using it jointly.

11. The rural land that does not gain heir pursuant to provisions of sub article 1,5 or 6 of this article, shall registered as vacant land, be distributed to the new petitioners.

18. የይዞታና የመጠቀም መብትን በስጦታ ስለማስተላለፍ

1. ማንኛውም የመሬት ባለይዞታ፣ የይዞታም ሆነ የመጠቀም መብቱን በክልሉ ውስጥ ለሚኖርና ቅድመ ሁኔታዎችን ለሚያሟላ ሰው በስጦታ ለማስተላለፍ ይችላል፤

ሀ. ተቀባዩ በግብርና ሥራ የሚተዳደር ወይም ለመተዳደር የሚፈልግ የክልሉ ነዋሪ ሆኖ ምንም አይነት መሬት የሌለው ወይም አስቀድሞ በያዘው መሬት አነስተኛነት ምክንያት ሌላ መሬት እየተከራየ የሚያርስ ልጅ ወይም የልጅ ልጅ ወይም ሌላ የቤተሰቡ አባል ከሆነ፤

ለ. ተቀባዩ የባለይዞታውን መሬት እያረሰ ወይም ሌላ ሥራ እየሠራ ስጦታው ከመከናወኑ በፊት ላሉት 3 ተከታታይ አመታት ሰጭውን በነፃ ሲጦር መቆየቱ የታወቀ ከሆነ፤

2. ማንኛውም የመሬት ባለይዞታ የይዞታ መብቱን በቋሚነት በግብርና ሥራ ለመተዳደር ለሚፈልግ የቤተሰብ አባል በስጦታ ማስተላለፍ ይችላል። እንዲሁም ለተወሰነ ጊዜ የመጠቀም መብቱን ለተለያዩ ሰዎች በስጦታ ሊያስተላልፍ ይችላል፤

3. የመሬት ይዞታው የባልና ሚስት የጋራ ወይም የሌሎች ሰዎች የጋራ ይዞታ በሚሆንበት ጊዜ ስጦታው የሚፀናው ባልና ሚስቱ ወይም ሌሎች የጋራ ባለይዞታዎች ሁሉም ከተስማሙ ብቻ ይሆናል፤

**18. TRANSFERRING POSSESSION AND USE RIGHT IN GIFT**

1. Any holder may transfer his holding or using right in donation to a person who resides in the region and fulfils the preconditions.

a. Where the donee is child or grand child or other family member engaged or like to be engaged in agricultural works, being the resident of the region and not holding any land or tills land by renting from others due to his previous small holding

b. Where the donee had stayed tilling the land of the holder or working other works and known free, and lived for 3 consecutive years before the gift is undertaken.

2. Any land holder may transfer permanently his holding right to family members and temporarily to various persons members in gift.

3. Where the land holding is a joint holding of a husband and wife or other persons, the gift shall only be applicable in agreement of all the husband and wife or other joint holders.

4. የይዞታ መብታቸውን ሣይጨምር ድርጅቶች በመሬት የመጠቀም መብታቸውን ለተወሰነ ጊዜ ለባለስልጣን መሥሪያ ቤቱ በማሳወቅ በስጦታ ማስተላለፍ ይችላሉ፤

5. ማናቸውም የገጠር መሬት የስጦታ ስምምነት በጽሁፍ መደረግ አለበት። በቃል የተደረገ የስጦታ ስምምነት በሕግ ተቀባይነት አይኖረውም፤

6. በጽሁፍ የተደረገ ማናቸውም የስጦታ ስምምነት መሬቱ በሚገኝበት ወረዳ ላለው የባለሥልጣኑ ቅርንጫፍ መስሪያ ቤቱ ቀርቦ መመዝገብ አለበት፤

19. በመሬት የመጠቀም መብትን በኪራይ ስለማስተላለፍና የግብር አወሳሰን

1. ማንኛውም አርሶ አደር በይዞታው ስር ያለውን መሬት የቤተሰብ ስምምነት መኖሩን ሲያረጋግጥ ወይም በጋራ ይዞታ ላይ ደግሞ የአባላቱ ይሁንታ ሲረጋገጥ የማከራየት መብት አለው።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም በግብርና ለመተዳደር የሚፈልግ ሰው የገጠር መሬት የመከራየት መብት አለው፤

4. Organizations may, excluding holding right, transfer land using right for limited period of time by notifying to the Authority.

5. Any rural land gift agreement shall be in writing, an agreement made orally shall not be acceptable by law.

6. Any gift agreement made in writing shall be submitted to and registered in the Woreda branch office of the Authority.

**19. TRANSFERRING USE RIGHTS IN RENT**

1. Any peasant under his holding shall have the right to rent where there is a family agreement made or in joint holding, the holders may show their agreement upon it.

2. Without prejudices to provisions of sub-article 1 of this article, anyone who likes to engage in agricultural works shall have the right to rent the rural land

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት አርሶ አደሮች መሬት በማከራየት መብታቸው ውስጥ ከይዞታቸው ሊያከራዩ የሚችሉት የመሬት መጠን፣ የኪራይ ውልና አይነት፣ የኪራይ ዘመን፣ የለምነት ደረጃ እና ዝርዝር መብትና ግዴታዎችን እንዲሁም ሌሎች ተዛማጅነት ያላቸው ጉዳዮች መካተታቸውን በሚመለከተው አካል መረጋገጥ አለበት፤ ዝርዝር አፈጻጸሙ በሚወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

4. ማንኛውም የመሬት ባለይዞታ አርሶ አደር የመጠ ቀም መብቱን ለማንኛውም ሰው በኪራይ ማስተላለፍ ይችላል፤

5. ማናቸውም የመሬት ኪራይ ስምምነት በጽሑፍ መደረግ አለበት፤

6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 መሠረት በጽሁፍ የተደረገ የመሬት ኪራይ ስምምነት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 የተደነገጉትን ዝርዝር ነገሮች የሚገልጽ ካልሆነ በስተቀር ፈራሽ ይሆናል፤

7. የሚከራየው መሬት በጋራ የተያዘ ከሆነ ሁሉም ባለይዞታዎች ካልተስማሙበት እና ከሚመለከተው የባለስልጣኑ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ቀርቦ ዝርዝር ሁኔታዎች ተሟልተው እስካልጸደቁ ድረስ ውሉ ፈራሽ ይሆናል፤

8. በጽሁፍ የተደረገ ማናቸውም የመሬት ኪራይ ስምምነት መሬቱ በሚገኝበት ወረዳ ላለው የባለሥልጣኑ ቅርንጫፍ መ/ቤት ወይም ህጋዊ ወኪል ቀርቦ መመዝገብ ይኖርበታል፤ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፡፡

3. According to sub article 1 of this article peasants in their right to rent land shall make the area of the land they want to rent, the agreement type year of the rent and detail rights and obligations as well as other related items, shall be ensured by the pertinent body. Detail shall be determined by the regulation

4. Any peasant holder may transfer his using right in rent to any person.

5. Any land rent agreement shall be made in writing

6. According to sub article 5 of this article agreement made in writing by the provisions stated under sub-article 3 of this article shall be invalid unless it indicates detail items in the contract.

7. Where the land to rent is held jointly, unless the joint holders agree upon it, and no detail item is fully submitted to the branch Authority for approval it shall be invalid.

8. Agreement made in writing shall be submitted to and registered in the Woreda branch office or legal agent. The detail shall be determined by the regulation.

9. በአንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 1 ረ የተደነገገው የኪራይ ዘመን ጣሪያ የውሉ ዘመን ሲያበቃ እንደገና ሊታደስ የሚችልበትን እድል የሚከለክል አይሆንም፤

10. ከግል ባለይዞታዎች ጋር በሚደረግ የመሬት ኪራይ ስምምነት የሚከፈለው የኪራይ መጠን አከራይና ተከራዩ በሚያደርጉት ድርድር የሚወሰን ይሆናል፤

11. በኪራይ ስምምነቱ ውስጥ እንደገና የማከራየት መብት ያለው መሆኑ በግልጽ ካለተመለከተ በስተቀር ተከራዩ መሬቱን በከፊልም ሆነ በሙሉ ለሶስተኛ ወገን ሊያከራየው አይችልም፤

12. ከዚህ አዋጅ በፊት ያሉ የገጠር መሬት ኪራይ ባህላዊና የጽሁፍ ውሎች ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፡፡ ነገር ግን ቀደም ሲል በባህላዊና በጽሁፍ ውሎች አማካኝነት የውል ስምምነት የገቡ ባለጉዳዮች በዚህ አዋጅ መሠረት የማስተካከያ ስራ እንዲያከናውኑ ይደረጋል፤ ዝርዝር አፈጻጸሙ በደንብ ይወሰናል፡፡

13. የገጠር መሬትን በጋራ ለማልማት የመሬት ባለይዞታው በመሬቱ የመጠቀም መብቱን ይዞ ከባለሃብቱ ጋር በሚገባው ውል መሠረት የልማት ሥራ ሊሰራ ይችላል፡፡ ውሉም አግባብ ባለው ባለስልጣን ጸድቆ መመዝገብ አለበት፤

9. The provision stated under sub-article 1, f of article 20 shall not ban the renewability of the agreement after the compleition of the contract period.

10. When the agreements during rent is made to private holders the amount of rent to be paid shall be made between the lesser and the lessee.

11. Unless it is clearly indicated in the rent agreement that the lessee has right to rerent, one shall, partially or fully, not rent the land to the third party.

12. Customary rural land lease contracts privately in future shall not have applicability. However, those who engage and made agreement priory shall be made correction by this proclamation. The details shall be determined by the regulation.

13. A land holder may, using land use right undertake development, jointly with an investor in accordance with the contract he concludes. Such contracts shall be approved and registered by the competent authority.

14. ማንኛውም አርሶ አደር በይዞታው ሥር ያለውን መሬት ሊያከራይ የሚችለው የምግብ ዋስትናውን በማይጎዳ መልኩ ሲሆን ብቻ ነው። ለዚህም ይረዳ ዘንድ በአቅራቢያው ባለው ባለሙያ ድጋፍ ማግኘት አለበት፤

15. የገጠር መሬት በሊዝ የተከራየ ባለሃብት ወይም አርሶ አደር የመጠቀም መብቱን እንደዋስትና ለማስያዝ ይችላል፤

16. የገጠር መሬት መጠቀሚያ የግብር ክፍያ እንደመሬቱ ስፋት፣ የመሠረተ ልማት መስፋፋት፣ የአየር ንብረት ሁኔታ፣ እንዲሁም የመሬቱ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ የመሳሰሉት ታሳቢዎችን መሠረት በማድረግ የሚወሰን መሆን አለበት፤ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል።

17. የገጠር መሬት መጠቀሚያ ግብር አወሳሰን እንደ አስፈላጊነቱ ጥናትን መሠረት በማድረግ በየጊዜው የሚታደስ ሲሆን አፈጻጸሙም የሚመለከታቸው መ/ቤቶችና አካላት በአዋጅ ስልጣን ከተሠጠው የመንግስት አካል ጋር በመሆን የሚከናወን ነው፤

14. Any peasant may, possibly do a land rent if it is not affecting the food security. Such cases shall be assisted by local professionals

15. An investor or peasant who has leased rural land may present use right as collateral.

16. The manner in which tax is to be paid on rural land shall be determined by the area of the land, level of fertility, available infrastructure, suitable weather as well as economic benefit of the area. The detail shall be determined by regulation.

17. The amount of tax to be paid on rural land based on study, shall be renewed and the authority vested with power shall execute in collaboration with competent bodies.

## 20. የገጠር መሬት ኪራይ

### 1. በግል የሚደረግ የመሬት ኪራይ

በአንቀጽ 19 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የገጠር መሬት ኪራይ በሚከናወንበት ጊዜ፡-

ሀ. ተዋዋይ ወገኖች በውላቸው ስለተፈጥሮ ሃብት ጥበቃና እንክብካቤ በተመለከተ ግዴታዎች በግልጽ ሊያስቀምጡ ይገባል፡፡ ለሚከሰተው ጉዳትም ሃላፊነት የሚወስድ ወገን ተጠያቂነት በተመለከተ መገለጽ አለበት፤

ለ. የሚከራየው መሬት የመስኖ መሬት ከሆነ የመስኖ ውኃ አጠቃቀም በሚመለከት የሚወጡ ደንቦች ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል፤

ሐ. በአከራይና በተከራይ መካከል የሚፈጸም ውል የኢትዮጵያ ፍትሐብሄር ሕግ የውል ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል፤

መ. ከሁለት ዓመት በላይ የሚደረግ የመሬት ኪራይ ውል ከልማዳዊ እርሻ ውጭ የማይጠቀም ከሆነ ተቀባይነት አይኖረውም፤

ሠ. በተዋዋይ ወገኖች የሚወሰን ቢሆንም መሬት በኪራይ የያዘ ሰው በመሬቱ የሚገኙ የሙጫ ዛፍንና ሌሎች ቋሚ ዛፎችን ፍሬዎች የመጠቀም መብት ሊኖረው ይችላል፤

ረ. የኪራይ ዘመንን በተመለከተ በባህላዊ አስተራረስ ዜዴ በሚጠቀሙ አርሶ አደሮች መካከል የሚደረገው የኪራይ ዘመን እስከ 2 ዓመት ሲሆን ለዘመናዊ የግብርና ቴክኖሎጂ ተጠቃሚዎች እስከ 10 ዓመት ይሆናል፤

ሰ. የመሬት ኪራይ ውል በሚከናወንበት ጊዜ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተሩ በአንቀጽ 8 በንዑስ አንቀጽ 4 መሠረት ተፈጻሚ ይሆናል፤

## 20. RURAL LAND RENT

### 1. Private Land Rent

Without prejudice to article 19 of the proclamation when rent shall to be made:

a. The agreed parties shall be clearly stated the obligation about the natural resource protection and conservation. It also indicates the responsible party which held accountable for the damage occurs to it.

b. If the rent to be made is on irrigable land the regulation to be issued on irrigation water utilization shall be applied.

c. The contract to be made between the lessees and lesser shall be implemented according to Ethiopian Civil code contract provisions.

d. Any rural land contract for traditional farming is shall not be more than two years.

e. Although it will be determined by agreed party, any person who holds land with rent shall have the right to use permanent crops like gum and other fruit of permanent trees.

f. Duration of land leases between the peasant and the lease shall be up to two years for traditional farming and ten years for users of modern technology.

g. When land lease contract made, the holding certificate shall be applicable. According to sub article 4 of article 8 of this proclamation.

## 2. በመንግስት የሚደረግ የመሬት ኪራይ

ሀ. በገጠር መሬት ኢንቨስትመንት ለማካሄድ የሚፈልግ ማንኛውም ባለሃብት ወደፊት ባለስልጣን መሥሪያ ቤቱ በጥናት ላይ ተመስርቶ በደንብ እስኪወስን ድረስ በክልሉ ለኢንቨስትመንት ተግባር የሚሆን የገጠር መሬት አጠቃቀም ለማሻሻል በወጣው ደንብ ቁጥር 29/2001 መሠረት የገጠር መሬት በኪራይ ሊያገኝ ይችላል። ሆኖም ሥነ ምህዳሩ በከፍተኛ ሁኔታ በተጎዳባቸውና በአስጊ ደረጃ ባሉ አካባቢዎች ለሚከናወኑ ተግባራት ሆነው ከስነ ህይወት ጥቅማቸውአኳያ እናከአካባቢ ጥበቃ አንፃር ጉልህ ድርሻ ለሚያበረክቱ ስራዎች እንደ ሃገር በቀል ዛፍ ዝርያዎች ልማት፣ መኖ ልማት እና መሰል ተግባራት መሬት በነፃ ሊሰጥ ይችላል፤ ዝርዝር አፈጻጸሙ በደንብ ይወሰናል።

ለ. ለኢንቨስትመንት በኪራይ የሚሰጥ መሬት አርሶ አደሩ በወል፣ በጋራ እና በግል ለግጦሽ፣ ለእርሻ፣ ለደን እና ለተለያዩ አገልግሎቶች ከሚጠቀምባቸው የይዞታ መሬቶች ነጻ መሆን አለበት፤

ሐ. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 (ለ) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ለኢንቨስትመንት በኪራይ የሚሰጥ መሬት የተሻለ ጠቃሚነት አለው ተብሎ ካልታመነበት በስተቀር የአርሶ አደሩ ይዞታ፣ ዛፎችና የተፈጥሮ ሃብትን በማይጎዳ መልኩ መሆን አለበት፤ ይህ ሳይሆን ቀርቶ ባለይዞታው ከይዞታው የሚነሳበት ወቅት አስፈላጊውን ማካካሻ ከሚመለከተው አካል የማግኘት መብቱ የተጠበቀ ነው፤

**2. Land lease by government**

a. Any investor who would like to engage in rural land investment shall get Land leases according to the investment rural land usage regulation No 29/2001. However, in the ecosystem already damaged and those in critical Condition, for endogenous tree development and the likes activity land shall made lease free. The detail to be determined by the regulation

b. Any land to be leased for investment shall be free from peasant holding owned individually, communally and group for agriculture, forestry and the like’s activity undertaking in it.

c. Without prejudice to sub article 2(b) of this article, land to be leased out for investment unless there is a strong belief that it has a better benefit the manner shall not to damage the peasant holding, trees and natural resources. However if any one lost his holding because of this, there is a right for compensation to made by concerned bodies.

መ. የገጠር መሬት ሊከራይ የፈለገ ባለሃብት ከሚመለከተው አካል የኢንቨስትመንት ሴርተፊኬት እና የተለያዩ ደጋፊ ማስረጃዎችን በማቅረብ ይሁንታ ካገኘ በኋላ እና በተጨማሪም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 (ለ) ከተደነገጉት መሬቱ ነጻ ሲሆን ባለሃብቱ የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ሰነድ ለባለስልጣን መሥሪያ ቤቱ አቅርቦ በማስጸደቅ ሥራውን በዚሁ መሠረት ማከናወን አለበት፤ ዝርዝር አፈጻጸሙ በደንብ ይወሰናል፡፡

ሠ. የገጠር መሬት በሊዝ የተከራየ ባለሃብት የተፈጥሮ ሃብት አጠቃቀምና አያያዝን በተመለከተ በአንቀጽ 22 በተጠቀሱት ዝርዝር ግዴታዎች አማካኝነት ተፈጻሚ ይሆናል፤

ረ. ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጠቀሜታ አይሎ ሲገኝ መንግስት በአርሶ አደሩ ያልተያዘውን መሬት የአካባቢውን ስነ ምህዳር በማያናጋ መልኩ በሊዝ ሊያከራየው ይችላል፤

ሰ. ወደ ፊት የአጠቃቀም እቅዱ ተግባራዊ ሲደረግ የሚወሰን ሆኖ የአጠቃቀም እቅዱ ተግባራዊ እስኪደረግ ድረስ ግን ለኢንቨስትመንት የሚውል የገጠር መሬት ከፍተኛ የመሬት ኪራይ ዘመን በየአምስት ዓመቱ በሚታደስ መልኩ እስከ 40 ዓመት ሊደርስ ይችላል፤ ዝርዝር አፈጻጸሙ በደንብ ይወሰናል፡፡

ሸ. ባለስልጣን መሥሪያ ቤቱ ከሚመለከታቸው አካላትና በተዋረድ ከሚዋቀሩ የባለስልጣኑ ቅርንጫፍ መ/ቤቶች እና ኮሚቴዎች ጋር በመሆን የኢንቨስትመንት መሬት በመለየት ለባለሃብቶች ዝግጁ በማድረግ ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፤

ቀ. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2, ሸ መሠረት በየቀበሌው የተዘጋጀውን መሬት የሚመለከተው አካል ባለሃብት ሲያስማራ የቀበሌ እና ንዑስ ቀበሌ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴዎች ከወረዳው የባለስልጣኑ ተጠሪ መሥሪያ ቤት ጋር በመሆን ይዞታውን ለባለሃብቱ ያስረክባሉ፤ የርክክብ ሰነዱንም ለሚመለከታቸው አካላት ያሰራጫል፤

d. Investors who insist rural land in lease shall submitte investment certificate and other documents and land is free from the provision stated under sub article 2, g of this article along with enviromenal impact assessment document which is presented to the Authority for approval. The detail determined by the regulation.

e. Investors who get rural land by lease shall have the obligation to conduct Article 22 stated for natural resource use and management.

f. When economic and social benefits prevail, the government may lease the Land not occupied by the peasant in the manner that is not affecting the ecology.

g. Until it will determine when the land use plan is implemented, the Maximum duration of rent time for rural land investment is 40 years. This shall renew in 5 years.

h. The authority with competent organ, respective branch offices to be established and committee shall identify land to be ready for investors.

i. In accordance with the sub article 2, h of this article, the land ready to investors whom allowed by competent organ which shall be done By the kebele and subkebele land administration and use committees along with the woreda authority branch office. The agreement shall distribute to the competent bodies

በ. በአንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ባለስልጣን መሥሪያ ቤቱ በሊዝ ለኪራይ ለዋለው የገጠር መሬት የተለያዩ የውል ዝርዝር ተግባራትን ባካተተ መልኩ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር በማዘጋጀት ይሰጠዋል፤

ተ. ባለሃብቱ ሙሉ ወጪውን ሲሸፍንም ባለስልጣን መሥሪያ ቤቱ የይዞታ ካርታ በማዘጋጀት ለባለሃብቱና ለሚመለከታቸው አካላት ያሰራጫል፤

ቸ. ከመንግስት ከሚመለከተው አካል በሊዝ የገጠር መሬት የተከራየና ውል በመግባት ወደ ሥራ የተሰማራ ባለሃብት የኪራይ ዘመኑን ሲያጠናቅቅ እንደአስፈላጊነቱ ውሉን በአዲስ መልክ እንዲዋዋል ይደረጋል፤ ዝርዝር አፈጻጸሙ በደንብ ይወሰናል፡፡

ኀ. ማንኛውም የገጠር መሬት ሊያለማ የፈለገ ኢንቨስተር ከመንግስት ጋር በሚደረገው ስምምነት መሠረት ዝርዝር የኪራይ ውል ይዘታ፣ የተከራይና አከራይ መብትና ግዴታዎች ጭምር ያካተተ መሆን አለበት፤ ዝርዝሩ በደንብ ይገለፃል፡፡

ነ. ኢንቨስተሩ በገባው የገጠር መሬት ውልና የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ሠነድ መሠረት ግዴታውን ካልተወጣ ይህንን አዋጅ ተከትሎ በሚወጣ ደንብ የሚወሰን ሆኖ ከይዞታ መሬቱ እስከማስለቀቅ የሚደርስ እርምጃ ይወሰዳል፡፡ በመሬቱ ላይ ለደረሰ ማንኛውም ጉዳት ባለሃብቱ ካሳ እንዲከፍልም ይደረጋል፤ የካሳ አከፋፈል እና ሌሎች ዝርዝር ጉዳዮች በደንብ ይወሰናል፡፡

j. In accordance with sub article 1 of article 27, the authority shall prepare and give the holding certificate in a manner that includes detail contract items in it.

k. The authority shall prepare holding map in which the investor cover the Cost to it and shall distribute to the investor and competent bodies.

l. Investor who rented rural land in lease and undertaking the activity as per the contract may renew the contract when the effected period of the lease ends. The detail shall determined by regulation

m. The agreement to made by between the investor and the government, rural Land development shall include the type of lease, right and obligation of the lessee and lesser.

n. If the investors fail to meet the obligation according to the contract Concludes including environmental impact assessment, it will be decided by the regulation to be issued following this proclamation in which Measures up to expropriating from the land shall be taken and Compensation has to make for the damage. Compensation payment and other details will determined by regulation.

ኘ. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2, ቸ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ውሉን መንግስት ለህዝብ ጥቅም ብሎ የሚያቋርጥ ከሆነ ለባለሃብቱ በጽሑፍ በማሳወቅ ንብረቱን እንዲያነሳና በመሬቱ ላይ ላፈራው ቋሚ ንብረትም ካሳ በመክፈል ውሉን ሊያቋርጥ ይችላል፤ የካሳ አከፋፈል ሁኔታው እና ሌሎች ዝርዝር ጉዳዮች ይህንን አዋጅ ተከትሎ በሚወጣ ደንብ ይወሰናሉ፡፡

አ. በገጠር መሬት ላይ ለሚከናወኑ እንደ አሸዋ፣ ድንጋይ፣ ኖራ፣ አፈር፣ ባህላዊ ወርቅ ቁፋሮ እና ወዘተ የማዕድን ማምረት ስራ ላይ የተሰማራ ማንኛውም ግለሰብ ወይም ድርጅት የአካባቢ ጉዳት እና የሃብት ብክነት በማያስከትል መልኩ ማከናወን አለበት፡፡ ይህ ሳይሆን ቀርቶ ለሚደርስ ጉዳት መልሶ የመገንባት ግዴታ አለበት፤ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፡፡

ከ. ይህ አዋጅ ተግባራዊ ከመደረጉ በፊትና በማናቸውም ሁኔታ የባለሃብቱን የማልማት አቅም እና አካባቢያዊ ደህንነትን ከግምት ውስጥ ያላስገቡ ማናቸውም የገጠር መሬት የኢንቨስትመንት ስራዎች ደረጃ በደረጃ በጥናትና በሕግ አግባብ ላይ በተመሠረተ አኳኋን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን እንዲስተካከሉ ይደረጋል፤

o. Without prejudice to the provisions of sub article 2, L of this article, when the government terminates the contract for the sake of public interest, it will be notify the investor by writing to remove the property and shall be made compensation for the permanent property raised on the land. The compensation to be made and other detail shall be determined by regulation to be issued following this proclamation.

p. Any one undertakes activities on rural land like, sand, stone, limestone, soil, traditional gold digging and the likes on rural land shall carry out in accordance in a manner that is not affecting the environment and loss of the resource. If the damage occurs, there will be an obligation for rehabilitation. The detail will be determined by the regulation.

q. Rural land investment activities carried out without consideration of investor development capability and environmental concerns, prior the proclamation, shall made correction step by step by study and appropriate law jointly with competent bodies.

**21. በሊዝ ሥርዓት የተገኘ በገጠር መሬት የመጠቀም መብትን የዕዳ ዋስትና አድርጐ ስለማስያዝ**

1. የገጠር መሬት በሊዝ የተከራየ ባለሃብት የመጠቀም መብቱን እንደዋስትና ለማስያዝ ይችላል፤
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በተደነገገው መሠረት የገጠርን መሬት በሊዝ የተከራየ ማንኛውም ባለሃብት የሊዝ ዘመኑ ፀንቶ ለሚቆይበት ጊዜ በተከራየው መሬት ላይ ያለውን የመጠቀም መብት ወይም በመሬቱ ላይ ያፈራውን ሃብት ወይም ሁለቱንም ባለስልጣኑ መሥሪያ ቤት እና የሚመለከተው አካል ካረጋገጠ በዕዳ ዋስትናነት ለማስያዝ ይችላል፤ ዝርዝር አፈጻጸሙ በደንብ ይወሰናል፡፡
3. ተቃራኒ የውል ቃል ከሌለ በስተቀር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት በመሬት የመጠቀም መብት በዕዳ ዋስትናነት ከተያዘ በመሬቱ ላይ የለማው ሀብትም አብሮ እንደተያዘ ይቆጠራል፡፡ ሆኖም በመሬቱ ላይ የለማው ሀብት ተነጥሎ በዕዳ ዋስትናነት የሚያዝ ቢሆን በመሬት የመጠቀም መብቱ አብሮ እንደተያዘ አያስቆጥረውም፤
4. የዕዳ ዋስትና ሆኖ የተያዘን በመሬት የመጠቀም መብት ባለገንዘቡ አስቀድሞ ካልተስማማ በስተቀር የአበዳሪውን ጥቅም በሙሉ ወይም በከፊል በሚጐዳ ሁኔታ በኪራይ ማስተላለፍ፣ በሌላ መሬት መለወጥ ወይም በሌላ ሁኔታ የይዞታ ለውጥ ማድረግ አይቻልም፤
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት በሊዝ ሥርዓት የተገኘ የገጠር መሬት የመጠቀም መብት በእዳ ዋስትናነት ሲያዝ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተሩ ባለይዞታው እጅ እንዲቀመጥ ይደረጋል፡፡ ከመንግስት ጋር በገባው ውል መሠረትም ባለይዞታው አስፈላጊውን ሁሉ የማሟላትና በወቅቱ የመፈጸም ግዴታ አለበት፤
6. በመሬት የመጠቀም መብትን በዕዳ ዋስትናነት የማስያዝ ስምምነት በጽሁፍ መደረግ አለበት፡፡ የስምምነቱ መግለጫ ጽሁፍም መሬቱ በሚገኝበት ወረዳ ላለው የባለሥልጣኑ ተጠሪ ጽ/ቤት ቀርቦ ካልተመዘገበ በስተቀር በ3ኛ ወገኖች ላይ መቃወሚያ ሆኖ ሊቀርብባቸው አይችልም፤

**21. Mortgage of rural land use right obtained in lease system**

1. An investor who has leased rural land may present his use right as collateral.
2. According to the provision of the sub article 1 of this article any investor who has leased rural land may secure as mortgage right to use his land or an asset produced on it or both for effective period of the lease if it is approved by the authority and competent bodies.
3. Unless there is a contrary agreement, where the land uses right is mortgage pursuant to sub article 2 of this article, the asset developed on the land shall be considered as it is with held together. However, where only an asset produced on land is mortgage, the land use right shall not be considered as mortgage together with same.
4. Unless the creditor priory agrees, it may not be possible to transfer the right to use the land obtained by mortgage in rent, change by another land or change the holding with any onther situation that may harm the creditor fully or partially.
5. When rural land obtained in lease systemsecured as a mortgage right to use land, the holding certificate shall remain to the holders according to the deal concludes with the government, the holders have the obligation to fulfill everything important and shall execute in time.
6. An agreement to secure land use right as mortgage shall be made by righting unless the clarification the agreement is submitted to a register in branch office of the authority where the land is found, it shall not affect the right of third party.

7. በዚህ አዋጅ መሠረት በመሬት የመጠቀም መብት ወይም በመሬቱ ላይ የለማ ሃብት በዕዳ ዋስትናነት ሊያዝ የሚችልበት የጊዜ ገደብ በሁለቱ ወገኖች የሚወሰን ሆኖ በአንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 2, ሰ ከተደነገገው ጣሪያ ዓመት ሊበልጥ አይችልም፤

## 22. የገጠር መሬት ተጠቃሚ ግዴታዎች

1. ማንኛውም የመሬት ተጠቃሚ በዚህ አዋጅ መሠረት ከዚህ በታች የተመለከቱት ግዴታዎች ይኖሩበታል፤

ሀ. በይዞታው ሥር ያለውን ወይም በኪራይ የተሰጠውን መሬት የመንከባከብና አካባቢውን የመጠበቅ እንዲሁም በሚወጣለት የአጠቃቀም እቅድ መሠረት ለታሰበለት አላማ እንዲውል ማድረግ፤

ለ. የፌዴራል የደን ሃብት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 452/1999 እንደተጠበቀ ሆኖ በመሬቱ አካባቢ እና በይዞታው ሥር በተፈጥሮ የበቀለ ዛፍ ከሌለ ደግሞ ዛፎችን የመትከልና በተገቢው ሁኔታ ተንከባክቦ የመጠበቅና የማሳደግ ግዴታ አለበት፡፡ በተጨማሪም በእርሻ ይዞታ ሥር ሆነው በተዳፋት ቦታዎች የሚገኙትን በተፈጥሮ የበቀሉ እናት ዛፎችን በሄክታር ቢያንስ በቁጥር 100 እና በሜዳማ አካባቢዎች ደግሞ በቁጥር ከ60-70 በይዞታው ላይ መተው፤

ሐ. የመሬት ተዳፋትነታቸው ከ30 በመቶ በታች የሆኑ መሬቶችን በተመለከተ የአፈር ክለትን የሚቀንስና ውሃ የመሰብሰብን ስልት የተከተለ አሰራር እንዲኖር የሚያስችል የመሬት አያያዝ መተግበር፤ ዝርዝር አፈጻጸሙ በደንብ ይወሰናል፡፡

7. In accordance to this proclamation, the right to use land or the duration to mortgage the resource developed on the land, though, it will determine by the two parties, shall not exceed the limited year stated under sub article 2, g of article 20 of the proclamation.

## 22. Obligation of rural land user

1. Any land user shall, pursuant to this proclamation, have obligations indicated here In under;

a. to protect and the land under his holding or land obtained in rent and Conserve the surrounding as well as apply according to the issued use Plan for the intended objective.

b. without prejudice to the proclamation number 452/1999 on federal forest Development, conservation and use, if there are no naturally grown trees in Their holding, they have the obligation to plant, preserve and manage the Trees. in addition, under the agricultural holding, 100 naturaly Grown mother shall left where as in plain areas it would be 60-70 per hactare

c. The management of rural lands for the slops less than 30%, shall follow the Strategy of soil conservation and water harvesting, the detail shall be determined by the regulation.

መ. የመሬት ተዳፋትነታቸው ከ31 በመቶ እስከ 45% በመቶ የሆኑ መሬቶችን ለአመታዊ ሰብሎች ልማት ለማዋል ይቻል ዘንድ ጠረጴዛማ እርከን ወይም ሌሎች ተስማሚ የአፈር ጠበቃ ሥራዎችን የማከናወን፤ እንዲሁም ተዳፋትነታቸው ከ45% በመቶ በላይ የሆኑ የገጠር መሬቶች ለእርሻና ለልቅ ግጦሽ እንዳይውሉ ሆነው ለዛፍ፣ ለቋሚ ተክሎችና ለእንስሳት መኖ ልማት እንዲውሉ የማድረግ፤

ሠ. በእርሻ ይዞታ ሥር እና በአካባቢው ያሉ ምንጮችና ውሃ አዘል መሬቶች ተገቢ ባልሆነ አስተራረስ ሳቢያ እንዳይጎዱ ጥንቃቄ የማድረግ፤

ረ. ወሰናቸው የተከለለ መሬቶችን ድንበር ያለመጋፋትና ተለይተው የሚታወቁ መንገዶችን ያለመዝጋት እንዲሁም ከአጎራባች ባለይዞታዎች መሬት ላይ ጉዳት ያለማድረስ፤

ሰ. መሬቱ በሚወጣለት የአጠቃቀም ዕቅድ መሠረት እንዲጠቀም አግባብ ባለው አካል በጽሁፍ ሲጠየቅ ተግባራዊ የማድረግ፤

ሸ. በይዞታው ሥር እና በአካባቢው የሚገኙ የዱር እንስሳት፣ አእዋፋት፣ በመመናመን ላይ የሚገኙና ከፍተኛ ጥበቃ የሚያስፈልጋቸው የእፅዋት ዝርያዎች እንደ ዋንዛ፣ ዞቢ፣ የቆላ ወይራ፣ ቀረሮ፣ ዝግባ፣ ኮሶ እና የመሳሰሉትን በአጠቃላይ ብዝሃ ህይወቱ እንዳይጎዳ ተገቢውን ጥንቃቄ የማድረግ፤

ቀ. መሬቱ እንዲለካ፣ የቅየሳ ሥራ እንዲካሄድበት፣ የአካባቢ ተፅዕኖ ኦዲት እንዲደረግበት አግባብ ባለው አካል ሲጠየቅ ለዚሁ ተግባር የመተባበር፤

d. For the slopes between 31-45%, annual crops development may be allowed. In rural land through making bench terraces and other suitable soil conservation practices. However for the slope more than 45%, rural lands shall not be used for farming and free grazing; it shall be used for development of trees, perennial plants and forage production.

e. The agricultural holding, spring areas and wetlands have to protect from damage due to improper handling of farming.

f. Delineated land and close road shall not be violated and not make any damage on neighboring land holding.

g. Land shall be utilized in accordance with a land use plan requested by competent authorityin writing.

h. Maximum protection of wild animal, birds and endangered plant species such as cordea, aningeria, olea, karero, podocarpes, Hygienia and The likes in general, the biodiversity which are harbored in his holding and locality.

i. Any one has the obligation to corporate with pertinent body when requested for measuring or undertaking surveying and Environmental Impact Assessment on the land.

በ. የመሬቱ ባለይዞታ ከሆነ የባለይዞታነት ማረጋገጫ ደብተር በሚሰጥበት ጊዜ የማውጣት፣ በጥንቃቄ የመያዝ፣ የማደስ፤

ተ. የመሬት ይዞታ መብቱን በሚያጣበት ጊዜ የተሰጠ ውን የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር አግባብ ላለው አካል የመመለስ፤

ቸ. በዝናብ ለሚለማ ይዞታ መሬቱ በወንዝ ዳር ወይም በገደል አካባቢ የሚገኝ ማንኛውም ተጠቃሚ ከዋና ወንዝ ዳር ከ500 ሜትር በላይ፤ ከውሀ አካላት 50 ሜትር እንዲሁም ከገደል ወይም ከቦረቦር ጥልቀቱን ታሳቢ በማድረግ ከ 10 ሜትር በላይ አርቆ የማረስ እና የተለያዩ የአፈርና የውሃ ጥበቃ ሥራዎችን እንደ እርከን በመስራት የአፈር ክለትን የመከላከል ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል

ኀ. ማንኛውም በገጠር መሬት የመጠቀም መብት የተሰጠው አካል የይዞታ መሬቱን የመጠበቅና የመንከባከብ ህጋዊ ግዴታ እንዳለበት፤

2. ማንኛውም የመሬት ተጠቃሚ የሆነ የግል ባለሃብት ወይም ድርጅት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ከተደነገጉት ግዴታዎች በተጨማሪ ለተፈቀደለት መሬት የአጠቃቀም እቅድ አቅርቦ የማስፀደቅና በእቅዱ መሠረት መሬቱን ጥቅም ላይ የማዋል ግዴታ አለበት። የሚያቀርበው የአጠቃቀም እቅድ የህብረተሰቡን ጤንነት፣ የአካባቢውን ደህንነትና የመሬቱን ለምነት መጠበቅ የመሳሰሉትን ግምት ውስጥ ያስገባ መሆን ይኖርበታል፤

j. To take, hold and renewed a certificate where there is a landholder and a land holding certificate issued.

k. Return the holding certificate; when depraved farm holding right.

l. Any land user under rain feed agriculture shall have an obligation to plough the land more than 500 meter far from main river, 50meter from water bodies and more than 10 from gully and also applied soil and water conservation works like terracing to avoid soil degradation. The detail detrmined by the regulation.

m. Anybody that has the right to use rural land shall oblige to protect and conserve the holdings.

2. Any private investor or organization, besides obligation provided under sub
Article 1 of this article, shall submit and cause approval of land use plan, and use the land in accordance with the approved plan. The plan to be submitted shall consider the health of the society, environmental concerns and the fertility of the land.

3. መሬቱን በመንከባከብና አካባቢን በመጠበቅ ረገድ አርአያነት ያለው ሥራ ለሚያከናውኑ የመሬት ባለይዞታዎችና ተጠቃሚዎች ባለሥልጣኑ አቅሙ በፈቀደ መጠን የማበረታቻ ሽልማት ይሰጣል፤

4. የአካባቢን ሥነ ምህዳር የሚያናጉ ሃገር በቀል ያልሆኑ የእፅዋት ዝርያዎች ሆነው ነገር ግን የኢኮኖሚ ጠቀሜታቸው የጎላ ድርሻ ያላቸውን እንደ ባህርዛፍ ያሉትን የእፅዋት ዝርያዎች ከእርሻ መሬቶችና ከውሃ ሃብት ምንጮች በማራቅ በጥናት በተመረጡ ቦታዎች እንዲተከሉና አማራጭ ገቢ እንዲያስገኙ የማድረግ ግዴታ አለበት፤

5. እያንዳንዱ ባለይዞታ በተለያዩ ምክንያቶች የተነሳ በሚጠቀምበት የይዞታም ይሁን በአቅራቢው በሚገኝ የተፈጥሮ ሃብት ላይ በሰደድ እሳት አማካኝነት ጉዳት እንዳያደርስ ከፍተኛ ጥንቃቄ የማድረግና የመከላከል ግዴታ አለበት፤ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፡፡

6. በባህላዊም ሆነ በዘመናዊ መንገድ በገጠር መሬት ላይ ለሚከናወኑ የማዕድን ማምረት ሥራዎች እንደ አሸዋ፣ ድንጋይ፣ ኖራ፣ አፈር፣ ወርቅ ቁፋሮ እና ይመሳሰሉት የማዕድን ማምረት ስራ ላይ የተሰማራ ማንኛውም ግለሰብ ወይም ድርጅት የአካባቢ ጉዳት እና የሃብት ብክነት በማያስከትል መልኩ እንዲያከናውን የሚመለከታቸው አካላት የመቆጣጠር ህጋዊ ግዴታ አለባቸው፤

3. The authority shall, as much as it can, motivate prize for the landholders and users who perform exemplary activities in land conservation and environmental conservation.

4. Those exotic plant species like eucalyptus which seriously affects the ecology but have huge economic benefit shall plant distance agricultural lands and shall grow in appropriate site.

5. Every holder, in his holding or vicinity shall have the obligation to take a maximum care and protect the natural resource from forest fire damage. The detail determine by regulation.

6. Traditional or modern mining activities such as sand, stone, lime, soil, gold digging and the likes, undertake on rural land by private or organization shall be in a manner that is not making any damage on the environment and loss of the resource. The competent bodies shall have the obligation by law to monitor/ regulate their activities.

23. ግዴታን አለመፈፀም ስለሚያስከትለው ኃላፊነት

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 22 የተደነገገውን የትኛውንም ግዴታ ወይም ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣው ደንብ የተደነገገውን ተመሳሳይ ግዴታ ያላከበረ የመሬታ ባለይዞታ የቃልና የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ተከታትሎ ይሰጠዋል፤

2. በተሰጠው ማስጠንቀቂያ መሠረት ስህተቱን ሊያርም ያልቻለ እንደሆነ ከዚህ በታች በተደነገገው መሠረት አስተዳደራዊ እርምጃ ሊወሰድበት ይችላል፤

ሀ. በራሱ ድክመት መሬቱን ባለመንከባከቡ ምክንያት በመሬቱ ላይ ጉዳት ከደረሰ የመጠቀም መብቱን መሬቱን ለመንከባከብ ግዴታ ለሚገባ ሌላ ሰው ለተወሰነ ጊዜ በኪራይ እንዲሰጥ የሚተላለፍ ውሣኔ ይሰጣል፤

ለ. ከዚህ በላይ የተመለከተው እርምጃ ተፈፃሚ ከሆነ በኋላ ጥፋቱ በተመሳሳይ ሁኔታ ከተደገመ በመሬት የመጠቀም መብቱን ለተወሰነ ጊዜ ከማገድ ጀምሮ ካሣ ሳይከፈል መሬቱን እንዲለቅ እስከመገደድ የሚደርስ እርምጃ ይወሰዳል፤

3. ማንኛውም የወል መሬት ተጠቃሚ መሬቱን ለመንከባከብ ከሕብረተሰቡ ጋር አልተባበረም ካለ ህግ ባለማክበሩ ምክንያት እንደቅደም ተከተሉ የቃል ወይም የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ እንዲሰጠው ወይም እንዲደርሰው ይደረጋል፤

**23. Effects of non-performance of obligations**

1. Land holder who failed to respect any obligations provided under article 22 of this proclamation or similar provisions or a regulation be issued to exclude this proclamation shall be oral and written respectively.

2. Where the holder tool to correct the mistakes in accordance with the notice, administrative measures may be taken as provided here in under;-

a. Because of his weakness where the absence of conservation Lead to the degradation of land, the decision shall be passed to transfer His right to use land in rent temporarily for a person who would like to take an obligation.

b. Where the offence is committed again after the measure indicated here in above is executed, a measure from suspending him from for a limited time up to expropriating from the land without making any compensation.

3. Where any communal land user refuses to corporate with the community to conserve the land, he shall respectively, be given oral or written notice for his refusal.

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ሥር የተደነገገው ማስጠንቀቂያ ከተሰጠው በኋላ ጥፋቱ በተመሳሳይ ሁኔታ ከተደገመ የወል መሬቱን እንዳይጠቀምበት ለተወሰነ ጊዜ ከማገድ ጀምሮ ለዘለቄታው በወል መሬቱ እንዳይጠቀምበት እስከመከልከል የሚደርስ ቅጣት ሊወሰንበት ይችላል፤

5. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 22 የተደነገጉትንና ሌሎች ግዴታዎች ያላከበረ የመሬት ተጠቃሚ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 እና ሥር ከተመለከቱት እርምጃዎች በተጨማሪ ለደረሰው ጉዳት በፍትሐብሔር ሕግ መሠረት ካሣ እንዲከፍል ሊወሰንበት ይችላል፤

6. በአንቀጽ 22 የተደነገጉትን ኃላፊነቶችና ግዴታዎች ባልተወጡ የገጠር መሬት ባለይዞታ ወይም ተጠ ቃሚ በሆኑ መንግሥታዊ መ/ቤቶች ወይም መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የብዙሃን ማህበራትና የሃይማኖት ተቋማት ወዘተ... ላይም እንደየአግባብነታቸው ተፈፃሚ ይሆናሉ፤

**24. ጥብቅና የተከለሉ ደኖች፣ ጨፌያማና ረግረጋማ መሬቶች**

1. ለደን፣ ለዱር እንስሳት፣ ለአፈር ጥበቃና ልማት፣ እንዲሁም ለማዕድን ልማት ጠቀሜታ የተከለሉ መሬቶች ከአጠቃላይ ሥነ-ምህዳር ይዞታቸው ጋር በዘላቂነት እንዲጠበቁ ይደረጋል፡፡ እነዚህ የተጠበቁና የተከለሉ አካባቢዎች በሚመለከተው ወይም አግባብ ባለው አካል በሚወጣው ደንብ መሠረት ይተዳደራሉ፤

4. Where the offence is committed again after the measure indicated here in above is executed, a measure from suspending him from for a limited time up to expropriating from using the communall land without making any compensation.

5. A land user who did not respect other obligations provided under article 22 of this proclamation, shall made pay compensation for the damage pursuant to civil code in addition to

6. Responsibilities provided in article 22 shall, upon failure to carry out obligations be applicable on rural land holder or user, government offices, NGO, civic societies and religious institution, as it may be appropriate.

**24. Reserved and protected forest, wet lands**

1. Lands demarcated for forest, wild life, and soil conservation as well as for mining development and historical use shall be preserved sustainably with their general ecological content. These demarcated and preserved areas shall be governed by the regulations to be issued by pertinent bodies.

2. ጥብቅ መሬቶችን የመከለል፣ የመለየት፣ የማልማት፣ የማስጠበቅ፣ መልሶ የማቋቋምና የመያዝ ተግባር በመንግስትና በአካባቢው ሕብረተሰብ ተሳትፎ ይከናወናል፤

3. የአካባቢው ሕብረተሰብ ከጥብቅ ደኖች ከሚገኘው ጥቅም ተካፋይ የመሆን መብቱ የተከበረ ነው፤

4. ጨፌያማና ረግረጋማ ውኃ አዘል ሥፍራዎች፣ ምንጮችና ሐይቆች አደጋ ላይ ከሚጥሉዋቸው የመሬት አጠቃቀምና ድርጊቶች ሁሉ ይጠበቃሉ፤

5. የአፈር መሸርሸርን ለመግታትና ብሎም የውኃ አካላትን ከደለል ለመከላከል የውሃ ዳርቻዎችና ዙሪያዎች በተስማሚ የእጸዋት ዝርያዎች መሸፈንና መከለል ይኖርባቸዋል፤

6. ጨፌያማና ረግረጋማ ውኃ አዘል መሬቶችን ለመጠበቅ የሚያስችሉ የተፋሰስ የልማት ሥራዎች በመንግስትና በማህበረሰቡ ተሳትፎ በጋራ መከናወን ይኖርባቸዋል፤

7. በዚህ አንቀጽ የተጠቀሱትን በመጣስ ጥብቅና የተከለሉ ደኖች፣ ጨፌያማ ረግረጋማ መሬቶችን መያዝ ፈጽሞ የተከለከለ ነው፤

2. The activity of demarcation, identification, development, preservation, rehabilitation and management of the preserved lands shall be carried out by government and participation of the community.

3. The right of local community to benefit from the preserved forest area shall be respected.

4. Marshy, swampy, spring areas and lakes shall be protected from any in appropriate land use activities that damage land.

5. Areas around water bodies shall be covered by suitable vegetation to protect soil erosion and sedimentation.

6. Water bodies' development activities enabling the protection of wet lands shall be carried out by the government and participation of the community.

7. It is strictly prohibited to use wet lands in contradicting the provisions stated under this article.

## ክፍል አራት

## የገጠር መሬትን ስለመለካት፣ ስለመመዝገብና ስለይዞታ ማረጋገጫ ደብተር

### 25. መሬትን ስለመለካት

1. ለተጠቃሚዎች በይዞታነት የተሰጠ የግል ወይም የጋራ፣ በአንድ አካባቢ ማህበረሰብ አማካኝነት በወል መጠቀሚያነት የተያዘ ወይም ለደን ልማት ወይም ለሌሎች መሠል ተግባራት የተከለለ የትኛውም የገጠ ር መሬት በባህላዊ ወይም በዘመናዊ የቅየሳ መሣሪያ በባለሥልጣኑ እና በተዋረድ በሚዋቀሩት የባለስልጣኑ ተጠሪ ወይም ቅርንጫፍ መ/ቤቶች አማካኝነት ተለክቶ ካርታ ይዘጋጅለታል፡፡ በዚህም ሣቢያ እያንዳንዱን መሬት በግልጽ ለመረዳት የሚያስችል የመሬት ልዩ ቁጥር አሰጣጥ ሥርዓት ተቀርጾ በሥራ ላይ ይውላል፡፡ የመሬቱን ድንበር የሚያሳይ ምልክትም በመሬቱ ላይ ይደረጋል፤
2. ማናቸውም መሬት በሚለካበት ጊዜ በተቻለ መጠን የሚለካው መሬት አዋሳኝ ባለይዞታዎች ወይም ተጠ ቃሚዎች በስፍራው እንዲገኙና ድንበራቸውን በስምምነት እንዲወስኑ ጥሪ ይደረግላቸዋል፡፡ የመሬቱ ቅየሣ የሚካሄደውም የባለይዞታዎችን ማሣዎች በመነሻነት በመጠቀም ይሆናል፤

## Part Four

## Measuring, Registering Rural Land and Holding Certificate

### 25. Land Measurment

1. Rural land given users in holding privately or in group, held for common usage by the community of an area, or forestry development, or conserved for any other similar activities shall be measured and the map shall be prepared by the authority in traditional way or modern tool. Because of this, a special system of enumeration shall be designed and implemented to clearly understand each land. The sign that indicate the boundary shall also be made on the land.
2. When any land is measured, the neighboring land holder or user shall, as much as possible, be called to attend there in and decide up on their boundary in agreement. The survey on the land may be conducted by using the plots of holders as a starting point.

3. በመሬቱ አለካክና በድንበሩ አከላለል ረገድ ቅሬታ የተሰማው ባለይዞታ ቅር የተሰኘበትን ምክንያት ገልጾ ይህንን አዋጅ ተከትሎ በሚወጣው ደንብ በሚወሰን የጊዜ ገደብ ውስጥ ጉዳዩ እንደገና እንዲታይለት በሚመለከተው አካል አቤቱታ ማቅረብ ይችላል፤

4. መሬቱ ከተለካ በኋላ በልዩ ልዩ ምክንያት መጠኑ ከተለወጠ እንደገና ተለክቶ በባለስልጣኑ አዲስ ካርታ ይዘጋጅለታል፤

5. ህጋዊ ፈቃድ ያላቸው የግል የቅየሣ ድርጅቶች በመሬት ቅየሣ ሥራው እንዲሳተፉ ሊደረግ ይችላል፤

6. ተለክቶ ከተሰጠው የይዞታ መጠን ውጭ ከሚመለከተው ህጋዊ አካል እውቅና ውጪ የይዞታ መጠኑን ያስፋፋ ወይም የለወጠ ማንኛውም ግለሰብ ወይም ድርጅት በህግ አግባብ እንዲጠየቅ ይደረጋል፤

**26. ስለመሬት ምዝገባና የመረጃ አያያዝ**

1. በዚህ አዋጅ መሠረት በባለሥልጣኑ የተለካ ማናቸውም መሬት በገጠር መሬት መመዝገቢያ መዝገብ ውስጥ ተመዝግቦ አግባብ ባለው ባለስልጣን ካርታ ይዘጋጅለታል፤

3. The land holder who complains regarding the land measurement and delineation, he may submit petition to the concerned body explaining his reason of complaints by the time limit to be decided by the regulation to be issued following this proclamation to make the case to be seen again.

4. Where for different reason, the area of the land is changed after it has been measured, it shall be measured again and a new map shall be prepared by the authority.

5. Private survey organization having a license may be made participate in land survey activity.

6. Any person or organization try to expand or change the holding area without the knowledge of responsible body shall be accountable by the relevant laws.

**26. Registration and data maintaining**

1. According to this proclamation, any land measured by the authority shall be registered in rural land and will have map prepared by the competent authority.

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የሰፈረውን ድንጋጌ ተፈፃሚ ለማድረግ የመሬት ምዝገባው የመሬቱን ባለይዞታ ሙሉ ስም፣ የመሬቱ ስፋት፣ ይዞታው የተገኘበትን ሁኔታ፣ የመሬቱ አጠቃቀም ዕቅድ እና ሽፋን፣ የመሬቱን አዋሳኞች፣ የለምነቱን ደረጃ፣ መሬቱ የሚውልበትን አገልግሎት እና ባለይዞታው ያለበትን መብትና ግዴታ የሚገልጽ መረጃ አካቶ መያዝ ይኖርበታል፤

3. በመሬቱ ላይ መብት ወይም ጥቅም እንዳላቸው ማስረዳት የሚችሉ ሰዎች ሁሉ አግባብ ላለው አካል ጥያቄ በማቅረብ ይህንኑ መዝገብ ማየት ይችላሉ፡፤

4. ከመሬቱ ጋር የተያያዘ ማናቸውም መብትና ግዴታን የሚመለከት ተግባር መሬቱ በሚገኝበት አግባብ ባለው ባለስልጣን ቀርቦ ካልተመዘገበ በስተቀር በሦስተኛ ወገን ላይ መቃወሚያ ሆኖ ሊቀርብ አይችልም፤

5. በሀሰተኛ መረጃ ላይ ተመስርቶ የተካሄደ ምዝገባ ሕጋዊ ውጤት አይኖረውም፤

6. የመሬት መመዝገቢያ መዝገብ በሁለት ቅጅ ተሠርቶ ዝርዝራቸው በደንብ በሚወሰነው አካላት እጅ ይቀመጣል፡፡ የመዝገቡ ማጠቃለያ ለባለሥልጣኑ ይላካል፤

2. To implement the provisions indicated under sub article 1 of this article, the land registration shall be carried out including the information explaining the full name of the holder, the size of the land, the condition of holding acquired, the right and duty of the holer.

3. Those people who can explain that they have the right or interest over the land, may submit their petition to the authority.

4. Unless any activity with regard to the right and obligation related to land is submitted and registered in local branch of the authority, it may not be an objection to the third party.

5. Registration carried out based on false information shall not have legal effect.

6. The land registration book shall be prepared in two copies and kept on the hands of the bodies whose detail shall be determined by regulation. The summary of the book shall be sent to the authority.

7. በመዝጋቢው ስህተት ምክንያት በማንኛውም ሰው ላይ ጉዳት የደረሰ እንደሆነ ስህተቱ የሚመለከተው የመንግሥት አካል በፍትሐብሔር ኃላፊነት ተጠያቂ ይሆናል፤

8. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 7 ድንጋጌ ተፈፃሚነት ምክንያት የሚመለከተው የመንግሥት አካል በስህተቱ ለተጐዳው ወገን ካሣ እስከመክፈል የደረሰ እንደሆነ ይህንኑ እንዲመለስለት ስህተቱን የሠራውን መዝጋቢ ሠራተኛ በተራው የመጠየቅ መብት ይኖረዋል:: ሆኖም መዘጋቢው በኃላፊነት የሚጠየቀው ስህተቱን የሠራው ሆን ብሎ ወይም በቸልተኝነት የሆነ እንደሆነ ነው::

9. በሊዝ ወይም በኪራይ የተያዘ የገጠር መሬት አግባብ ባለው አካል መመዝገብ አለበት፤

10. በወረዳዎች የሚገኙ የባለሥልጣኑ ቅርንጫፍ መ/ቤቶች የቀበሌ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴዎች የመሬት ምዝገባውን በአግባቡ እንዲያካሂዱ አስፈላጊውን እገዛ የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው፤

7. Where damage occurs on any person due to the fault of the registrar, the body of the government which is attributed with the fault shall be accountable to the civil liability.

8. Where the concerned government body approaches up to paying compensation to the victim due to the fault up on the implementation of provision of sub article 7 of this article, it shall have the right to claim from the registrar who committed the fault to reimburse the payment. However, the registrar will be liable when he commits the fault intentionally or negligently.

9. Any rural land that is held through lease or rent shall be registered by the competent authority.

10. The branch office of the authority in woredas shall have a responsibility to give the necessary support to the kebele land administration and use committees to properly carry out the land registration.

## 27. ስለመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ደብተር

1. የገጠር መሬት በይዞታ የተሰጠው ማንኛውም ሰው የመሬቱ ዝርዝር የተመዘገበበት የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር በስሙ ተዘጋጅቶና ፎቶግራፉ ተለጥፎበት በባለሥልጣኑ ይሰጠዋል፡፡ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር የባለይዞታው በሕግ የተጠበቀ መብት ማስረጃ ነው፡፡

2. መሬቱ የባልና ሚስት የጋራ ከሆነ የሁለቱም ተጋቢዎች ፎቶ ግራፍ ተለጥፎበት አንድ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ተዘጋጅቶ ይሰጣቸዋል፡፡ እንዲሁም በሌሎች በጋራ የተያዘ ከሆነ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተሩ የሁሉም የጋራ ባለይዞታዎች ስም ያለበት ሆኖ መዘጋጀት አለበት፤

3. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገጉት መስፈርቶች በይዞታ ማረጋገጫ ደብተሩ መካተት ይኖርባቸዋል፡፡

4. የመሬቱ ይዞታ ማረጋገጫ ደብተሩ በአንዱ ስም ተዘጋጅቶ ከተሰጠ በኋላ ጋብቻ ከተፈፀመ ተጋቢዎቹ መሬቱን የጋራ ይዞታ ለማድረግ ሊስማሙ ይችላሉ፡፡ ባልና ሚስት የግል የነበረውን መሬት በስምምነት የጋራ በሚያደርጉበት ጊዜ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተሩ የሚታደሰው ያለምንም ክፍያ በነፃ ይሆናል፡፡

## 27. Land Holding Certificate

1. Any person, granted rural land shall be given the land holding certificate in which the detail of the land is registered by the authority prepared by his name and photograph fixed there on. The holding certificate is a legal certificate of the holder.
2. Where the land is a holding of a husband and a wife in common, the holding certificate shall be prepared by the name of both spouses. If it is held communally it shall be prepared by the name of all communal holders.

3. The provisions indicated under sub article 2 of article 26 of this proclamation shall be included in the holding certificate.
4. When marriage is concluded after the certificate is given in the name of spouses, they may agree to make the land a common holding. Where the spouses make the land that was individual holding to a common holding, the holding certificate may be renewed freely, without any payment.

5. ተቃራኒ የጽሁፍ ማስረጃ ካልቀረበ በስተቀር የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር በስሙ የተሰጠው ሰው የመሬቱ ሕጋዊ ባለይዞታ እንደሆነ ይቆጠራል፤

6. በሕግ ከሚወሰነው የአንድ ማሳ ዝቅተኛ መጠን በታች የሆነ መሬት በይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ውስጥ ለብቻ አይመዘገብም። ሆኖም የዚህ አይነት መሬቶችን በተመለከተ የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ ተዘጋጅቶ የሚሰጥበት ሁኔታ ወደፊት በደንብ ይወሰናል፤

7. ያለበቂና ሕጋዊ ምክንያት በዚህ አዋጅ መሠረት ተፈላጊውን የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ሳያወጣ በገጠር መሬት ሲጠቀም የተገኘ ማንኛውም ባለይዞታ ከማስጠንቀቂያ ጀምሮ መሬቱን እስከማስለቀቅ እና የተፈጥሮ ሃብት ላይም ጉዳት ከደረሰ ተጠያቂ ሊያስደርግ የሚችል እርምጃ ይወሰድበታል፤ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል።

5. The person who is granted the land holding certificate in his name shall, unless a contradictory written document is submitted, be considered legal holder of the land.

6. The land which is less than the minimum limit of holding shall not be registered alone in the book of land holding certificate. However concerning such lands the preparation and the provision of land holding certificate shall be determined by a regulation.

7. Where any person found using rural land without taking the necessary rural land holding certificate, a measure starting from notice to displacing from land shall be taken. The detail shall be determined by regulation.

## 28. የይዞታ መሬትን ኩታ ገጠም ስለማድረግ

1. አርሶ አደሮች በመሃከላቸው በሚኖረው ፍላጎትና ፈቃደኝነት ላይ በተመሠረተ ስምምነት የይዞታ መሬት መራራቅንና መቆራረጥን በማያስከትል መልኩ የይዞታ ማሳቸውን ኩታ ገጠም እንዲያደርጉ ይበረታታሉ፤

2. በግል ይዞታ ሥር ያሉ መሬቶች ከመራራቃቸው የተነሣ የሚወስዱትን ጊዜና ጉልበት ከግምት ውስጥ በማስገባት በፈቃደኝነት የይዞታ መሬቶችን ኩታ ገጠም ማድረግና ለአሰራር እንዲያመች እንዲያደርጉ በተዋረድ በሚዋቀሩት አካላት በኩል ሰፊ የግንዛቤ ሥራ መከናወን አለበት፤

3. አርሶ አደሮች የተራራቁ ይዞታዎችን በስምምነት ኩታ ገጠም በሚያደርጉበት ጊዜ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተሩ እና ካርታው የሚታደሰው ያለምንም ክፍያ በነፃ ይሆናል፤

4. አነስተኛ ማሳዎች ለልማት አመቺ እንዲሆኑ በአርሶ አደሩ ሙሉ ፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የይዞታ መጠን ልውውጥ እንዲያደርጉ ይበረታታሉ፤

## 28. Making possession adjacent

1. Peasants, based on the will and consent, shall be encouraged to make their possession of farm land adjacent.

2. Lands under private holding, by considering the time and labor taken due to its fragmentation, the respective authority to be established shall undertake awareness activities in order to make their possession adjacent by consent and to make it suitable for application.

3. When peasants made their fragmented holdings adjacent by consent, land holding certificate shall be renewed without payment.

4. In order to make small farm plots convenient for development, farmers are encouraged to voluntarily exchange their holding by their full consent.

5. የይዞታ ልውውጥ ለማድረግ ፈቃደኛ የሆኑ ባለይዞታዎች ለመለዋወጥ ያሰቡትን የማሳ ስፋትና የለምነት ደረጃ በቀበሌው አስተዳደር ክልል ውስጥ የሚኖሩ ሌሎች አርሶ አደሮች እንዲያውቁት ለማድረግ የቀበሌ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴዎች እና በቀበሌው አስተዳደር አማካኝነት እንዲሰራጭ ይደረጋል፤

6. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 11 በተደነገገው መሠረት በህብረተሰቡ ጥያቄና ተሳትፎ የሚከናወን የሰፈራና የመንደር ምስረታ ፕሮግራም የመሬት ኩታ ገጠምነትን ዓላማ የሚያረጋግጥ መሆን አለበት፤

29. ልቅ የግጦሽ ስርዓትን ስለመግታት እና በወል ስለተያዙ መሬቶች

1. በወል ይዞታነት የሚታወቁ ጉብታዎች፣ የተጎዱ፣ የተራቆቱ፣ ምርታማ ያልሆኑ መሬቶች፣ በቀላሉ ሊጎዱ የሚችሉ ተዳፋትና ተራራማ አካባቢዎች በአግባቡ ለመጠቀም በህብረተሰቡ ተሳትፎ ላይ መሠረት ያደረገ የአያያዝና የአጠቃቀም እቅድ እንዲወጣላቸው ይደረጋል። በሚወጣው ዝርዝር ደንብ መሠረት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝና በህብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ሲያገኝ ወደ ግል ይዞታነት በመቀየር በተሻሻለ አሠራር ለግጦሽ፣ ለደንና ለሌሎች ቋሚ ተክሎች ይውላሉ፤

5. The information of the size and level of fertility of the farm plots which farmers intend to exchange holdings shall be distributed through kebeles land administration committees to let other farmers residing in the kebele know about it.

6. Resettlement and villagisation program to be undertaken at the request and participation of the community pursuant to sub article 11 of article 14, shall ascertain the objective of land consolidation.

29. **PROHIBITION OF GRAZING AND COMMUNAL LAND HOLDING**

1. The known communal possession of dams: damaged, degraded in fertile lands, slopy and mountainous areas shall use properly, management and utilization plan of those possessions shall be made based on the participation of the community. If necessary based on formulated detail regulations and accepted by the community such lands shall be changed into private possession and by using modern technique utilizing the land for grazing, forest and other perennial crops.

2. በክልሉ ውስጥ ያሉትን የወል የግጦሽ መሬቶች ደረጃ በደረጃ ወደ ግል ግጦሽ ይዞታነት እንዲቀየሩ ማስቻልና በተሻሻሉ የመኖ ዝርያዎች በመተካት የማምረት አቅማቸውን ማሳደግ ያስፈልጋል፤

3. የወል የግጦሽ መሬትን በመንከባከብ የማምረት አቅሙ እንዲያድግ ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል ባሳተፈ መልኩ መከናወን አለበት፤

4. በህብረተሰቡ የሚወጡና ይህን አዋጅ የማይቃረኑ የአካባቢ ሕጎችና ልማዳዊ አሰራሮች በወል መሬቶች አጠቃቀምና አያያዝ ላይ ተፈጻሚነት እንዲኖራቸዉ ይደረጋል፡፡

5. በወል መሬቶች ላይ የሚገኙትን እጽዋት፣ የዱር እንስሳት፣ አእዋፋትና ሌሎች የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ሀብቶችን እንዲሁም ታሪካዊ ቅርሶችን ሁሉም ዜጋ የመንከባከብ ሃላፊነት አለበት፤

6. ግጦሽና የመጠጥ ውሃ ፍለጋ ከአጎራባች ክልሎች በተለያዩ ምክንያቶች የሚደረገውን ህገ ወጥ የእንስሳት እንቅስቃሴ መስመር በማጥናት ደረጃ በደረጃ እልባት እንዲያገኝ ለማስቻል በተዋረድ ያሉ አካላት የቅርብ ግንኙነት በመፍጠር ይህንን አዋጅ ተከትሎ በሚወጣ ደንብ መሠረት ተፈጻሚነቱን ማረጋገጥ አለባቸው፤

2. Communal lands found in the region shall be changed into private grazing possession gradually and substituted by improved forest species in order to develop the potential of productivity.

3. The manner in which communal grazing land for the development of potential productivity shall be made by the participation of the community.

4. Local laws issued by the society, and customary practices, which are not contravening with the proclamation, shall be applicable on utilization of communal lands.

5. All citizens shall have the responsibility to protect wild animals, plants, birds and other natural and artificial resources and heritages found on the communally possessed land.

6. Illegal animal movement from neighboring region shall be made through study and made solution for grazing and drinking water; the respective authority shall create a close link and ascertain its execution on regulation to be issued following this proclamation.

7. ግጦሽና የመጠጥ ውሃ ፍለጋ ከአጎራባች ክልሎች የሚደረግ የእንስሳት እንቅስቃሴ መስመር በማጥናት የሚመለከተው አካል የክትባትና የቁጥጥር ስራ መስራት ይኖርበታል፤

## ክፍል አምስት
## ኃላፊነት ስላለባቸው አካላት

30. ስለልዩ ልዩ መሥሪያ ቤቶች ኃላፊነት

1. ባለሥልጣኑ በተዋረድ የሚዋቀሩትን አስፈጻሚ መ/ቤቶች የማደራጀት፣ አግባብ ያላቸውን አካላት በማስተባበርና በማቀናጀት አስፈላጊውን የሙያ ድጋፍ በመስጠት ይህንን አዋጅ የማስፈፀም ኃላፊነት አለበት፤ ዝርዝር ተግባሩ ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብ ይወሰናል።

7. By studying the animal movement route from neighboring region for grazing and drinking water, the competent organ shall undertake quarantine measures

## PART FIVE
## THE RESPONSIBLE BODIES

### 30. Responsibility of Various Offices

1. The authority shall have the responsibility in strengthening the institutions that are yet to be established in the respective authority and shall implement this proclamation by providing the necessary professional support and by coordinating and integrating the competent authorities. The detail mandate shall be determined by the regulation.

2. በክልሉ ውስጥ የሚገኙ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች እና የግል ተቋማት ከመሬት አጠቃቀም ወይም አጠባበቅ ጋር ግንኙነት ያለውን ማናቸውንም ሥራ በሚያከናውኑበት ወይም መሬትን ለተለያዩ ተግባራት በሚጠቀሙበት ጊዜ በዚህ አዋጅ የሰፈሩትን ግዴታዎች የመፈፀምና የማስፈፀም ኃላፊነት አለባቸው፤ ዝርዝር ተግባሩ በደንብ ይወሰናል፡፡

3. የወረዳና የቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤቶች ድንበራቸው በግልጽ እንዲካለል በማድረግ የአዋጁን ተፈፃሚነት በበላይንት የመመራት ኃላፊነት አለባቸው፡፡ ዝርዝር ተግባሩ ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፤

31. ስለባለሥልጣኑ የወረዳ ተጠሪ ጽ/ቤት ኃላፊነት

በወረዳ ደረጃ የሚቋቋመው የባለሥልጣኑ ተጠሪ ጽ/ቤት ይህንን አዋጅ በማስፈፀም ረገድ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

2. Government offices and private institutions found in the region shall have the responsibility to implement obligations stated in this proclamation while they carried out activities related to land use/ conservation detels shall be determind y the regulation.

3. The woreda and Kebele administration councils shall have responsibility to lead the implementation of the proclamation causing the clear delineation of their boundaries. The detail shall be determined by regulation.

**31. THE RESPONSIBILITY OF WOREDA ACCOUNTABLE OFFICE OF THE AUTHORITY**

The accountable office of the authority to be established at woreda level shall have the following duty and responsibility with regard to implementing this proclamation;

1. በባለሥልጣኑ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 42/1995 አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 3 እና በክልሉ የአስፈጻሚ አካላት አደረጃጀት፣ ስልጣንና ተግባር አዋጅ ቁጥር 56/1998 አንቀጽ 29 ንዑስ አንቀጽ 18 እና 19 ድንጋጌዎች በተሰጠው ስልጣን መሠረት በወረዳ ደረጃ የአካባቢ ጥበቃ፣ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽሕፈት ቤት፣ በቀበሌዎች እና በንዑስ ቀበሌዎች ደግሞ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴዎችን በሕዝብ ምርጫ በማቋቋም ከገጠር መሬት ጋር ተያያዥነት ያለውን ተግባር ያከናውናል፤ ሴቶች በነዚሁ ኮሚቴዎች በአባልነት ከወንዶች ጋር በተመጣጠነ ቁጥርም መመረጣቸውን ያረጋግጣል፤
2. በወረዳ የሚቋቋመው የአካባቢ ጥበቃ፣ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽሕፈት ቤት፣ በቀበሌና በንዑስ ቀበሌ ደረጃ የሚቋቋሙትን የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴዎችን ይከታተላል፣ የመሬት አስተዳደሩ ተግባር አዋጅ በሚጠይቀው መሠረት እየተካሄደ መሆኑን ይከታተላል፤ ዝርዝር አፈጻጸሙ በደንብ ይወሰናል፤
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በተደነገገው መሠረት ለተመረጡ የኮሚቴ አባላት ተግባርና ኃላፊነታቸውን አስመልክቶ ተገቢውን ሥልጠና ይሰጣል፤
4. በወረዳው የአካባቢ ጥበቃ፣ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀምን የሚመለከቱ መረጃዎችን በአግባቡ ይይዛል፣ ይጠብቃል፣ ያድሳል፣ ለሚመለከታቸው አካላትም ያሰራጫል፤
5. የወረዳው የአካባቢ ጥበቃ፣ መሬት አሰተዳደርና አጠቃቀም ጽሕፈት ቤት ተጨማሪ ዝርዝር ተግባርና ኃላፊነት በደንብ ይወሰናል፤

1. Land administration and use office at woreda level shall be established and land administration and use committee at Kebele and sub kebele shall elect through public election pursuant to provisions of subarticle 3 of article 9 of the proclamation number 42/1995 and sub article 18 and 19 of article 29 of proclamation number 56/1998 in which it insures the election of women to this committee membership shall be balanced.

2. The environmental protection and land administration and use office that are going to be established shall monitor the activity of Kebeles and subkebeles land administration and use committee being implemented as per the regulation.

3. Provide appropriate training to the committee member's elected pursuant to the provisions of sub article one of this article concerning their duties and responsibilities.

4. Information related to woreda land administration and use shall be properly handled, keeps, renewed and distributed to concerned bodies.

5. The mandate and responsibility of woreda environmental protection, land administration and use Authurity shall be determined by regulation.

**32. ስለቀበሌ እና ንዑስ ቀበሌ ወይም ጎጥ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴ**

1. በቀበሌ ደረጃ የሚቋቋም የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴ በቀበሌው ውስጥ ባለሥልጣኑ ከሚሰይመው ወይም ከሚመድበው ባለሙያ ጋር በመተባበር ይህንን አዋጅ በማስፈፀም ረገድ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፤

ሀ. በቀበሌው ውስጥ የሚገኘውን መሬት ያስተዳድራል፣ የመሬት አጠቃቀም በህዝብ ተሳትፎና በወረዳው የባለሥልጣኑ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ትብብር እንዲወሰን ያደርጋል፤

ለ. የሚቀርብለትን የመሬት ጥያቄ ተቀብሎ በሕዝብ ተሳትፎ እየታገዘ ቅደም ተከተል በማስያዝ እደላው የሚካሄድበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

ሐ. ከባለሥልጣኑ በሚሰጥ መመሪያ የቀበሌውን የመሬት ባለይዞታዎችና የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር የተሰጣቸውን ሌሎች ሰዎች መዝግቦ ይይዛል፤

መ. ማናቸውም የመሬት ድልድል፣ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር አሰጣጥ፣ አንድን ቦታ ለመንደር ምሥረታ የማዋል ተግባር፣ የወል መሬትን ለግል መጠቀሚያ የማከፋፈልና የአንድን መሬት አገልግሎት የመለወጥ ሥራ እንዲሁም ለህዝብ አገልግሎት ካልሆነ በስተቀር የመሬት ይዞታን ወይም የመጠቀም መብትን የሚያግድ ወይም የሚያሳጣ ማናቸውም ውሣኔ በቀበሌው ሕዝብ ተሣትፎ የተደገፈ መሆኑን ያረጋግጣል፤

**32. KEBELE AND SUKEBELE LAND ADMINISTRATION AND USE COMMITTEE**

1. The land administration and use committee to be established at kebele level shall, in collaboration with the professional assigned by authority in kebele, have the following duty and responsibility.

a. Administering the land found in the kebele, cause the decision of land use through participation of public and collaboration with the woreda branch office authority.

b. Facilitates conditions for land distribution by arranging order having received questions of land submitted to it and being helped by the public participation.

c. Register and keeps the land holders of the kebele and other persons land holding certificate according to a directive to be given by the authority.

d. Insure any decision that suspends or deprives the right to hold or use land is supported by the participation of the kebele people, unless it is for any land distribution, holding certificate provision, vilagization, and distribution of communal land for private use, exchange of the service of the land as well as public use.

ሠ. የቀበሌው የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴ ዝርዝር ተግባርና ኃላፊነት በደንብ ይወሰናል፤

2. የንዑስ ቀበሌ ወይም ጎጥ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት ይህንን አዋጅ ተከትሎ በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፤

ክፍል ስድስት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

33. መሬትን ለሕዝብ አገልግሎት ሰለማስለቀቅ

1. ባለሥልጣኑ የገጠር መሬትን ለሕዝብ አገልግሎት ለማዋል ከማንኛውም ባለይዞታ ወይም ተጠቃሚ ተገቢውን ካሣ በቅድሚያ ከሚመለከተው አካል በማስከፈል ማስለቀቅ ይችላል፤ ዝርዝር አፈጻጸሙ በደንብ ይወሰናል፤

2. ለሕዝብ አገልግሎት ለማዋል ይቻል ዘንድ የገጠር መሬት እንዲለቀቅ በባለሥልጣኑ የወረዳ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ከመወሰኑ በፊት መሬቱ የሚለቀቅበት ተግባር ከአካባቢው ሕብረተሰብ ልማት ጋር በቀጥታ የተቆራኘ ስለመሆኑ ጉዳዩ ለቀበሌው ሕዝብ ውይይት ቀርቦ የብዙሃኑን ድጋፍ ማግኘት አለበት፤

3. ማናቸውም የወረዳ አስተዳደር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የገጠር መሬት እንዲለቀቅ ሲወሰን ከባለሥልጣኑ የሚያገኘውን መረጃ መሠረት በማድረግ መሬቱ የሚለቀቅበትን ጊዜና የሚከፈለውን የካሣ መጠን ገልጾ ለመሬቱ ባለይዞታ ወይም ተጠቃሚ በጽሁፍ ማሣወቅ አለበት። በካሣው መጠን ቅር የተሰኘ ወገን ጉዳዩን ለባለሥልጣኑ የማቅረብና የማስመርመር መብት ይኖረዋል፤

e. The duties and responsibility of the kebele land administration and use committee shall be determined by regulations and directives.

2. The duties and responsibility of the sub-kebele land administration and use committee shall be determined by regulations.

**PART SIX**

**MISCELLANEOUS PROVISIONS**

**33. Expropriating land for public use**

1. The authority may expropriate rural land from holder or user for public service by paying proper compensation in advance. The detail shall be determined by regulation.
2. Where the land expropriation activity is directly related with the development of the surrounding society, the case shall be submitted to the kebele people for discussion and get majority vote, therein, before it is decided by the woreda branch office of the authority.

3 Where any woreda administration decide on the rural land to be expropriated pursuant to subarticle 1 of this article, it shall, based on the information from the authority, notify it in writing to the land holder or user stating the time of expropriating and the amount of compensation to be paid. The party who have complained on the amount of the compensation shall have right to submit the petition to the authority and get investigation thereof.

4. ለሕዝብ አገልግሎት የሚለቀቅ የገጠር መሬት የሚከፈለው የካሣ መጠን በኢፌዲሪ መንግስት ለህዝብ ጥቅም ሲባል የይዞታ መሬት የሚለቀቅበትንና ለንብረት ካሳ የሚከፈልበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 455/1997 መሠረት ተፈጻሚ የሚሆን ሲሆን ቀመሩም በደንብ ይወሰናል፤

5. የካሣው ከፋይ መንግሥት፣ የግል ድርጅት፣ ሕብረተሰብ ወይም ሌላ አካል ቢሆንም የይዞታውን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ ግን የካሣ ክፍያው መጠን ማስሊያ ቀመር ለከፋዩ አካል አንድ አይነት ይሆናል፤

34. አለመግባባቶች ስለሚፈቱበት ሁኔታና ስለባህላዊ ደንቦች ተፈፃሚነት

ማንኛውም ሰው አቤቱታውን ወደ መደበኛ ፍ/ቤት የማቅረብ መብቱ እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

1. ከመሬት ይዞታ ወይም ከመጠቀም መብት ጋር በተያያዘ የሚነሳ ማናቸውም አለመግባባቶች ቅድሚያ በሽምግልና ታይቶ በእርቅ እንዲፈቱ ጥረት መደረግ አለበት፤

2. የሽማግሌዎች አመራረጥና የእርቁ ድርድር አካሄድ የየአካባቢውን ባህላዊ ሥርዓትና ህግ መሠረት አድርጐ በባለጉዳዮች ስምምነት የሚፈፀም ይሆናል፤

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 መሠረት ክርክሩ ፍጻሜ ሊያገኝ ካልቻለ እንደ ጉዳዩ አግባብ ሥልጣን ላላቸው ፍርድ ቤት ወይንም የአስተዳደር አካል ቀርቦ በወረዳው የባለስልጣኑ ተጠሪ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት አስፈላጊውን መረጃ ተወስዶ እልባት እንዲሰጥ ይደረጋል፤

4. The amount of compensation to be paid for expropriation shall be made according to the proclamation number 455/1997 about compensation to be made for public interest. The formula of compensation shall be determined by regulation.

5. Eventhough, the compensation payer is government, private organization, community or other body, the calculating formula for compensation shall be the same by taking into account the holding socio-economic assumptions.

34. **Conflict Resolution and Applicability of Customary Laws**

Although, any person shall have the right to appeal to the court thereof:

1. Any dispute arise from land holding or using shall first resolve by arbitration

2. The election of arbitrators and the manner of arbitration shall base on the prevailing customary laws by the agreement of the parties.

3. If the arbitration fails to come up with the solution according to sub- Article 1 and 2 of this Article, shall present to justice Authorities based on the information obtain from the woreda responsible Authority/.

4. የአቤቱታዎችና ክርክሮች ውሳኔ አሰጣጥ ሂደት መራዘም እንዳይከሰት፡-

ሀ. የሴቶችና ሕፃናት መብት እንዳይጓደል ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸው አካላት ጉዳያቸውን የመከታተልና የተጠቀሱት መብቶች የማረጋገጥ ሃላፊነት አለባቸው፤

ለ. በክርክሩ መራዘም ምክንያት መሬቶች ጾም እንዳያድሩና የተፈጥሮ ሃብት ብክነት እንዳይደርስ ጉዳዩን የሚያዩት አካላት አስፈላጊውን እርምጃ የመውሰድ ኃላፊነት አለባቸው፤

35. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት ከመሬት ይዞታና ከመጠቀም መብት ጋር ተያይዘው በሌሎችሕጐች የተቋቋሙ መብቶችና ግዴታዎች ይህንን አዋጅ እስካልተቃረኑ ድረስ ተፈፃሚነታቸው ይቀጥላል፤

36. ስለቅጣት

ማናቸውም የመሬት ተጠቃሚ ይህንን አዋጅ ወይንም በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጣውን ደንብ ወይም መመሪያ ተላልፎ ቢገኝ አግባብነት ባለው ህግ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፤

37. የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም ሰው ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር የመተባበር ግዴታ አለበት፤

4. To avoid prolong litigation for Petition and appeal:

a. Bodies related women and children right shall have the responsibility to protect and ensure their right.

b. Competent bodies shall take every measure to avoid land with out cultivation and protect from loss f natural resource due to the prolong litigation.

**35. Transitory Provision**

Laws related to land holding and using right which issued previously by other laws shall be applicable, if it does not contradict this proclaimation.

**36. Penality**

Any land user shall be accountable by the existing law, if any body violates the regulation and directives to be issued by following this Proclaimation.

**37. Collaboration obligation**

Any person shall have the obligation to collaborate with implementation of this proclamation.

**38. ደንብና መመሪያ የማውጣት ስልጣን**

የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ደንቡ የማዉጣት ስልጣን ሲኖረዉ መመሪያዉን በተመለከተ ባለስልጣን መሥሪያ ቤቱ ሊያዘጋጅ ይችላል።

**39. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በክልሉ ምክር ቤት ጸድቆ በልሳነ ህግ ጋዘጣ ታትሞ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አሶሳ መጋቢት - ቀን 2002 ዓ.ም.**

**አህመድ ናስር አህመድ**

**የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት**

**ፕሬዝዳንት**

**38. The power to issue regulation and directive**

The regional administrative councile shall have the Authority to issue the regulation while the Authority shall make the directive.

**39. Effective Date**

This proclaimation shall come in to effect as of the date of it is publication in Lisan Hig Gazeta.

**Done at Assosa March, 2010**

**Ahmed Nasir Ahmed**

**President of the Benishangul Gumuz Regional State.**